አዲስ ዘመን

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 193 መጋቢት 13 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “መንግሥት በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የቀረበበትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ክስ በፍፁም አይቀበልም”

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ጦርነት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተከስቷል ሲል የደረሰበትን ድምዳሜ የኢትዮጵያ መንግሥት በፍፁም እንደማይቀበለው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት ባወጣው መግለጫ፣ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን በተመለከተ ያወጣው መግለጫ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና የተመድ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር በጋራ ካደረጉት ምርመራ አንፃር ሲታይ ምንም አዲስ ግኝት ያልተካተተበት ነው ብሏል። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያቀረበበትን ባዶ ውግዘት በፍፁም እንደማይቀበለው ገልጿል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ያወጣው መግለጫ አንድን ወገን ብቻ መወንጀል ላይ ያነጣጠረ መሆኑንም ነው ሚኒስቴሩ በመግለጫው የጠቆመው። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አማራጮችን ለመለየት ብሔራዊ ምክክር ለመጀመር

“ መንግሥት በአሜሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

# የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 2015 በሚያዚያ ወር መጨረሻ ላይ በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 2015 ከሚያዚያ 28 እስከ ግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በሚሊኒየም አዳራሽ እንደሚካሄድ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በማስጀመሪያ መርሐግብሩ ላይ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፣ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ለመጪዎቹ 10 ዓመታት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ነው።

ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ ለሌሎች መትረፍ እንደምትችል በስንዴ ምርት ላይ ታይቷል ያሉት አቶ መላኩ፤ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፉ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት ከተቋማት ጋር በመቀናጀት እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በአንድ ዓመት የሚቆም ሳይሆን ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት በልዩ ትኩረት

የኢትዮጵያ ታምርት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “ረመዷንን ስንፆም የተቸገሩትን በመርዳትና የታረዙትን በማልበስ ሊሆን ይገባል”

- ሼህ ሃጂ ኢብራሂም ቱፋ
የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ሙስሊሙ የዘንድሮውን የረመዷን ፆም ሲፆም የተቸገሩትን በመርዳትና የታረዙትን ወገኖች በማልበስ ሊሆን እንደሚገባ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሃጂ ኢብራሂም ቱፋ ጥሪ አቀረቡ፡፡

ሼህ ሃጂ ኢብራሂም ቱፋ የ 1444ኛውን የረመዷን ፆም በማስመልከት ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት፤ በረመዷን ጾም ወር ሕዝበ ሙስሊሙ ከወትሮ በበለጠ እርስ በእርሱ እንዲሁም ከሌሎች ወገኖቹ ጋር የሚረዳዳበት፣ ይቅር የሚባባልበት እና አቅመ ደካማ ወገኖቻችንን በተለያየ መልኩ አቅሙ በፈቀደው መርዳት

“ረመዷንን ስንፆም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር
DERBA CEMENT
በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY
የሚሰጡ አገልግሎቶች
- ለቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎት አቅራቢዎች ፈቃድ መስጠት
- የቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎቶችን መቆጣጠር
- የፍሪኩዌንሲ እና የቴሌኮም ቁጥር ሀብቶችን ማስተዳደር
- የቴሌኮም መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቅሬታ መፍታትና መብት ማስጠበቅ
- የዘርፉን ፍትሃዊ ተወዳዳሪነት ማበረታታት
- ሁሉን አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ታሪፍ መቆጣጠር
አድራሻ ከኤድናሞል ወረድ ብሎ ሮቤል ፕላዛ ህንፃ
+251-11-692-80-42 | contact@eca.et
9991 | https://www.eca.et
ጥራት ያለው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ እንጥራለን!

AMG STEEL FACTORY
ኤ.ኤም.ጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
Our Products
GI-Coil Color Coil Tiles
Ega Sky Tiles Corrugated Sheet Curving Ridge Sky Ridge V-Gutter Accessories
Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80/ 0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

AfriSky PLC
ETHIOPIA
Our Products
Billet RHS Wire Rod Re-bar CZU H-BEAM Nail Steel Structure Tanker
Akaki, Gelan
0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06



ፎቶ፡- ኢዮብ ተፈራ

አቶ ሽመልስ አብዲሳ

# የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ መሆኑ ተገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጻፈው የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ መሆኑ ተገለጸ።

የመደመር ትውልድ መጽሐፍ በኦሮሚያ ክልል ደረጃ በትናትትናው ዕለት በክልሉ ፕሬዚዳንት በአቶ ሽመልስ አብዲሳ፣ የፌዴራል እና የክልሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለሀብቶች፣ ተጋባዥ እንግዶች እንዲሁም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት የትውውቅ ፕሮግራም ተካሂዷል።

አቶ ሽመልስ እንደገለጹት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተጣበበ የሥራ ሁኔታ ውስጥ ሆነው የጻፉት ይህ የመደመር ትውልድ መጽሐፍ በትውልዶች መካከል የነበረውን መቃቃር በእጅጉ የሚቀርፍና ገቢው ሙሉ በሙሉ ለልማት መዋሉ ደግሞ ሌላኛው አስደማሚ ገጽታ ነው።

ኢትዮጵያውያን ያላቸውን ሀብትና ዕውቀት በመደመር ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ ደረጃ እንድትደርስ መጽሐፉ የተነተነበት አግባብ ለትውልዱ ትልቅ ቁም ነገር ያስጨብጣል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ በአንድነት ላይ ጽኑ አቋም የነበራቸውን ሼክ ሁሴንን ለማስታወስ የመጽሐፉ ገቢ በኦሮሚያ ደረጃ የሶፍዑመር ዋሻን ለማልማት መዋሉ ትልቅ ኩራት ነው ብለዋል።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ነጋ ወዳጆ በበኩላቸው፣ ሶፍዑመር ዋሻ በሚገባ መልማት ከቻለ ባሌን ብቻ ሳይሆን መላ ኢትዮጵያን የሚያኮራ ታሪካዊ ዋሻ መሆኑን ተናግረዋል።


የዓለም አገራት በቱሪዝም ዘርፍ ጠቀም ያለ ገቢ በሚያመነጩበት ወቅት ኢትዮጵያ በርካታ የቱሪስት መስህቦች እያሏት ባለመልማታቸው በርካታ ገቢ ማጣቷን የገለጹት አቶ ነጋ፣ ከዚህ አንጻር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የትውልዱን ማህበራዊ መስተጋብር ጥሩ መሠረት ላይ ከመጣል በተጨማሪ ለቱሪዝም ዘርፉ የሰጡት ትኩረት የሚያስደንቅና ቁጭትን የሚፈጥር ነው ብለዋል።

ሶፍዑመርን ለማልማት በሚሊዮን ብር የሚቆጠር ገንዘብ የሚጠይቅ መሆኑ ያነሱት አቶ ነጋ፣ ለዘርፉ ማሰብ አንድ ነገር ሆኖ በተጨባጭ ሃሳቡን ወደ መጽሐፍ በመቀየር ገቢ ማመንጨት መቻል ደግሞ ጀግንነት መሆኑን ገልጸዋል።

በትናንትናው መድረክ ብቻ መጽሐፉን ለመግዛት ቃል በተገባው መሠረት 609 ሚሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን የመጽሐፉ ሽያጭ በተለያዩ መድረኮች እንደሚቀጥል ለማወቅ ተችሏል።

# አፍሪካን ከድህነት ለማላቀቅ የማዕድናት ክምችትን እንደ ዕድል መጠቀም ያስፈልጋል

**ሞገስ ጸጋዬ**




አዲስ አበባ፡- አፍሪካን በዘላቂነት ከድህነት ለማላቀቅ በተፈጥሮ ሀብት ያላትን ከፍተኛ የማዕድናት ክምችት እንደ ዋና ዕድል መጠቀም እንደሚያስፈልግ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አስታወቀ። 55ኛው የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን የፋይናንስ፣ ፕላኒንግና ምጣኔ ሀብት ልማት የሚኒስትሮች ጉባዔ በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል።

በጉባዔው ማጠቃለያ ላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ጸሀፊ አንቶኒዮ ፔድሮ ለጋዜጠኞች በሰጡት ማብራሪያ፤ በአፍሪካ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በከፋ ድህነት ውስጥ እንደሚገኙ አንስተው፤ አህጉሪቷን በዘላቂነት ከድህነት ለማውጣት በተፈጥሮ ሀብት ያላትን ከፍተኛ የማዕድናት ክምችት እንደ ዋና ዕድል መጠቀም ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

በተጨማሪም አፍሪካን ከድህነት በማውጣት ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የግሉ ዘርፍ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ኢንቨስተሮች በተለያዩ የልማት ዘርፎች መሰማራት ይኖርባቸዋል ያሉት ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊው፤ አፍሪካን ወደ ዕድገት ጎዳና ለመምራት የሁሉም ሀገራት ቁርጠኝነት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣናን ማጠናከር ለጋራ ዕድገት አይተኬ ሚና አለው ያሉት አንቶኒዮ ፔድሮ፤ አህጉሪቷ ለያዘችው የዘላቂ ልማት ዕቅድ አስፈላጊና የጀርባ አጥንት መሆኑን አንስተዋል። አፍሪካ የ2063 አጀንዳን ለማሳካት ያሏትን ሀብቶች በቅንጅትና በአግባቡ መጠቀም፣ ድህነትን፣ ድንቁርናንና ግጭትን መቀነስ የዕለት ከዕለት ስራ መሆን እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ሁሉም ሀገራት አንድነትን በማጠንከርና ለጋራ አህጉራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማለም መስራት ይኖርባቸዋል። ጉባዔው አፍሪካ ያላትን ዕድል ያደሰንበትና እንዴት ከድህነት መውጣት እንደሚቻል የመከርንበት ነው ብለዋል።

እንደ ጸሃፊው ገለጻ፤ አፍሪካ ወደ ዘላቂ ልማት ለመግባት ያሏት አዎንታዊ ዕድሎች በርካታ ናቸው። ከዚህም ውስጥ በበርካታ የተፈጥሮ ሀብት ክምችትና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት አመቺ የሆነ አየር ንብረት ለውጥ ተጠቃሽ ናቸው። ያሉ ሀብቶችን በጋራ በመስራት ከድህነት ለመውጣት ልዩ አጋጣሚን ይፈጥራል።

በተለይም የማዕድናት ክምችትንና የደን ሀብቶችን ተጠቅሞ በቀላሉ ወደ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መግባት እንደሚቻል አስረድተው፤ የአፍሪካ አህጉር መስራት በሚችል ከፍተኛ በሆነ የስራ አቅም ባላቸው ወጣቶች የተሞላ በመሆኑ ይህንን ዕድል ይበልጥ በማልማት ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት መጠቀም ይገባል ብለዋል። ሀገራትም የወጣቶችን አቅም ለማሳደግ ፖሊሲዎችን በመቅረጽ ለጋራ ዕድገት መስራት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል።

# በአዲስ አበባ 70 በመቶ ያህል ተሽከርካሪዎች የወሰን ገደብ እየተሳለፉ ነው

**አዲሱ ገረመው**




አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ 70 በመቶ ያህል ተሽከርካሪዎች የወሰን ገደብ እየተላለፉ መሆኑና የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ በፍጥነት የማሽከርከር ወሰን ላይ ጠንካራ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ።

የጆንስሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳት ምርምር ተቋም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኅብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ከተማ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ የአሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪ ተጠቃሚዎችን የመንገድ አጠቃቀም የጥናት ውጤት ትናንት ይፋ አድርጓል።

በጥናቱም በከተማዋ በሰዓት ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሜትር ማሽከርከር የተፈቀደ ቢሆንም 70 በመቶ ያህል ተሽከርካሪዎች የወሰን ገደቡን የሚተላለፉ መሆናቸውንና፣ አደጋ የማድረስ ድርሻቸውም 59 በመቶ እንደሆነ ተገልጿል። በመዲናዋ በፍጥነት የማሽከርከር ወሰን ላይ ጠንካራ ቁጥጥር እንደማያስፈልግ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኅብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት ተመራማሪ ፕሮፌሰር ዋቅጋሪ ደሬሳ ላለፉት ሰባት ዓመታት በአዲስ አበባ ደረጃ በተካሄደው የመንገዶች የዳሰሳ ጥናት የተገኙ ቁልፍ ግኝቶችን በገለጹበት ወቅት፤ በመዲናዋ ለትራፊክ አደጋ መንስኤ የሆኑ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም በፍጥነት ማሽከርከር ከሁሉም በበለጠ አደጋን እያስከተለ ይገኛል ብለዋል።

ፍጥነት ከፍተኛ የአደጋ ስጋት የሚያስከትልና ለከባድ ጉዳት የማጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ዋቅጋሪ፤ በመካከለኛ የተሽከርካሪ ፍጥነት ላይ በሰዓት አንድ ኪሎ ሜትር ፍጥነት መጨመር አካል ጉዳት የመከሰት እድልን በሶስት በመቶ እንዲሁም የሞት የመከሰት ዕድልን ከአራት እስከ አምስት በመቶ እንደሚጨምር ነው የገለጹት።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ በአዲስ አበባ ውስጥ በአነስተኛና ውስጥ ለውስጥ እንዲሁም በመጋቢ መንገዶች የፍጥነት ወሰን በሰአት ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሜትር ነው። ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመሰል መንገዶች ከተቀመጠው 30 ኪሎ ሜትር በሰዓት ይበልጣል። በእነዚህ መንገዶች 70 በመቶ ተሽከርካሪዎች በፍጥነት ይጓዛሉ። ይህ አሃዝ ባለፉት ሰባት ዓመታት በተከታታይ ጨምሯል።

አሽከርካሪዎች ከስራ ቀናት ይልቅ በእረፍት ቀናት ፍጥነታቸውን በእጥፍ የመጨመር ዝንባሌ እንደሚታይባቸውም ተማራማሪው ገልጸዋል። ባለ ድርሻ አካላት የተጠናከረ የወሰን ቁጥጥር በማድረግ በትራፊክ አደጋ እየጠፋ ያለውን የሰው ሕይወት መታደግ እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የመንገድ ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ቢኒያም ጌታቸው በበኩላቸው፣ የጥናቱ ውጤት ውሳኔ ሰጪዎች፣ የመንገድ ደህንነት ባለሙያዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ሕይወትን መታደግ የሚያስችል የመንገድ ደህንነት ማሻሻያ ስራዎች እንዲሰሩ የመፍትሄ አቅጣጫ አመላክቷል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጭር እና የረጅም ጊዜ የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ ዕቅድ አውጥቶ ውጤታማ የማሻሻያ ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ መሰረተ-ልማት ግንባታ በተለይም አደጋ የሚበዛባቸው ቦታዎች ላይ የመንገድ ደህንነት የምህንድስና ማሻሻያዎችን ማድረግ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፣ የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ሥራዎች እና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ላይ እንዳለ ጠቁመዋል።

በከተማዋ የትኛውም አካባቢ በተለይ በውስጥ ለውስጥና በመጋቢ መንገዶች ሳምንቱን ሙሉ በፍጥነት ማሽከርከር ላይ ቁጥጥር እንዲካሄድ፣ ሁሉም ሞተረኞች የጭንቅላት መከላከያ ቆብን እንዲያደርጉና በትክክል እንዲያስሩ ቁጥጥር እንዲደረግ፣ ከኋላ ወንበር የሚቀመጡ ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ የመጠቀም ልምድን ለማሳደግ የቁጥጥር ስራ እንዲካሄድ፣ አሁን ያለውን የጭንቅላት መከላከያ ቆብ አጠቃቀም ሕግ በትክክል በማሰርና ባለማሰር በሚል ለይቶ በማስቀምጥ ሕጉ እንዲሻሻል ማድረግ እንደሚገባ ጥናቱ አመላክቷል።

የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው፣ ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር በአዲስ አበባ ውስጥ አሁንም ችግር እንደሆነ ቀጥሏል። የጭንቅላት መከላከያ ቆብን በትክክል የመጠቀም ልምድ በሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች 31 በመቶ ሲሆን፣ በተሳፋሪዎች ደግሞ 12 በመቶ ነው። በመዲናዋ 99 በመቶ የሚሆኑ አሽከርካሪዎች የደህንነት ቀበቶን የሚጠቀሙ ሲሆን፤ 84 በመቶ የሚሆኑት ከአሽከርካሪዎች አጠገብ የሚቀመጡ ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ ይጠቀማሉ። ከኋላ ወንበር ከሚሳፈሩት ውስጥ ደግሞ ስድስት በመቶ ብቻ የደህንነት ቀበቶ ይጠቀማሉ።

ከጾታ አንጻር የሴቶች የደህንነት ቀበቶ የመጠቀም ልምድ 40 በመቶ ሲሆን፤ ከአምስት ዓመት በታች ላሉ ህጻናት ስድስት በመቶ ብቻ የህጻናት የደህንነት መቀመጫ እንደሚጠቀሙ ተመላክቷል።

ከዚህም ባሻገር የፍጥነት ገደቦችን የመንገዶችን አይነትና አካባቢውን በተለይም የገበያ ማዕከላት፣ የንግድ አካባቢዎች፣ ትምህርት ቤቶችንና የመኖሪያ አካባቢዎችን መሰረት በማድረግ ማሻሻል እንደሚገባ ጥናቱ አመላክቷል። ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የመንገድ ተጠቃሚዎችን ከአደጋ ለመጠበቅ የአነስተኛ ፍጥነት መንገዶችን ለይቶ ማውጣትና የፍጥነት መቀነሻ ዘዴዎችን መስራት፣ በትራፊክ አደጋ መንስኤዎች ላይ የባህሪ ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ እና ከትራፊክ ቁጥጥር ጋር የተያያዙ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መስራት ሁነኛ መፍትሄዎች እንደሆኑም በጥናቱ ተጠቁሟል።

# በአማራ ክልል ስራ አቁመው የነበሩ 38 ሆስፒታሎች መሰረታዊ አገልግሎት እየሰጡ ናቸው

## - የህክምና ተቋማትን ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ ለማስገባት 13 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ በደረሰባቸው ጉዳት ሥራ አቁመው ከነበሩት 40 ሆስፒታሎች ውስጥ 38ቱ መሰረታዊ አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ የአማራ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን የህክምና ተቋማት የመልሶ ግንባታ እንዲሁም የህክምና መሳሪያዎችን አሟልቶ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ 13 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል።

የአማራ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አብዱልከሪም መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በክልሉ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ስራ አቁመው ከነበሩ 40 ሆስፒታሎች ውስጥ 38ቱ ወደ ስራ ገብተዋል። ወደ ስራ የገቡት ሆስፒታሎችም መሰረታዊ የሚባሉ አገልግሎቶችን እየሰጡ ናቸው። በዋናነት የእናቶችና ህጻናት ህክምና አገልግሎት፣ የድንገተኛ ህክምና እና የክትትል አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

ምክትል ኃላፊው እንደገለጹት፣ ወደ ስራ የገቡት ሆስፒታሎች የተወሰነ አገልግሎት ከመስጠት ውጪ ደረጃውን የጠበቀ የሆስፒታል አገልግሎት እየሰጡ አይደለም። ሆስፒታሎቹ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እና ጉዳት የደረሰባቸውን የህክምና ተቋማትን ወደ ስራ ለማስገባት በተደረገው የዳሰሳ ጥናትም 13 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተረጋግጧል።

የህክምና ተቋማት ሙሉ ለሙሉ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግም ከአጋር አካላት፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ እርዳታ ያስፈልጋል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

አቶ አብዱልከሪም እንደተናገሩት፣ በአሁኑ ወቅት በክልሉ 98 ሆስፒታሎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በተጨማሪ 917 ጤና ጣቢያዎች ሲኖሩ፣ ከ3 ሺህ 500 በላይ ጤና ኬላዎች በጤና ኤክስቴሽኖች አማካኝነት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል።

በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ በአማራ ክልል ጉዳት የደረሰባቸውን የጤና ተቋማት ለመገንባትና በግብዓት ለማሟላት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ክልሉ ማስታወቁ የሚታወስ ነው።

# ቢሮው በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 61 ሴት ተማሪዎች ሽልማት ሰጠ

**መዓዛ ማሞ**



አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ በመዲናዋ ለሚገኙ 61 ሴት ተማሪዎች ሽልማት ሰጠ።

የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ዓለምአቀፉን የሴቶች ቀን "እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ" በሚል መሪ ቃል በመዲናዋ ሲያከብር ቆይቶ የማጠቃለያ ፕሮግራም ባካሄደበት በትናንትናው ዕለት የቢሮው ኃላፊዋ ዶክተር ሀና የሺንጉስ፣ ዓለም አቀፉን የሴቶች ቀን በማስመልከት 500 እና ከዚያ በላይ ውጤት ላስመዘገቡ 61 ሴት ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸው የአምስት ሺህ ብር ሽልማት መበርከቱን ገልጸዋል።

በየትምህርት ቤቶች የሴቶች ክበቦች እንዲጠናከሩ መሰራቱን፣ ለሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ሞዴሶች እንዲደርሱ እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሴቶች በመለየት ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መደገፍ እንዲችሉ ለተስማሚ ቴክኖሎጂ በግዢ ከአምሥት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ እገዛ መደረጉን አብራርተዋል።

በተጨማሪም ቢሮው የሴቶችን ቀን ሲያከብር በ11ዱም ክፍለ ከተሞች የገበያ ትስስር ለመፍጠር ባዛሮች ተካሂደው ሴቶች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል ብለዋል። ሁሉም "እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ" የሚለውን መሪ ቃል ተግባራዊ በማድረግ ሴቶችን ከማንኛውም ጥቃት የመጠበቅ እና የመከላከል እንዲሁም ሴቶች በሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች ሁሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በሚሰሩት ስራ ውጤታማ እንዲሆኑ በማገዝና በመደገፍ ለሴቶች ያለንን ክብር በተግባር ማሳየት አለብን ሲሉም አሳስበዋል።

ዶክተር ሀና የሺንጉስ አክለውም፣ ሴቶች አንችልም የሚለውን ገደብ ትተን ከፊት በመቅደም እና ችግሮችን በማሸነፍ ከኋላችን ለሚመጡ ታናናሾቻችን ምሳሌ መሆን አለብን ብለዋል።

በዕለቱ ቢሮው ያዘጋጀላቸውን ሽልማት የተቀበሉት ተማሪ ሳሊሀ ሀጂ እና ተማሪ ሰላማዊት ገብረሀና ሽልማቱ የልፋታቸው ውጤት መሆኑን ገልጸው፣ ከስር ያሉ ታዳጊዎች የእነርሱን ፈለግ በመከተል ጠንክረው እንዲሰሩ የሚያበረታታ መሆኑን ገልጸዋል። በማጠቃለያ ፕሮግራሙ ለሴት የከተማ ጽዳት ሰራተኞች፣ መምህራን፣ የትራፊክ ፖሊሶች እና የጋሞ እናቶች እውቅናና ክብር ተሰጥቷል።

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግሉ ዘርፍ በግብርና እንዲሳተፍ ማበረታቻ ማቅረብ እንደሚገባ ተገለጸ

**ሄርሞን ፈቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የግብርናው ዘርፍ እንዲዘምንና በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ከተፈለገ የግሉ ዘርፍም እንዲሳተፍበት ማበረታቻ ማቅረብ እንደሚገባ ተገለጸ። በአዲሱ የግብርናና መሬት ልማት ፖሊሲ መሰረት መሬትን በዘመናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል ሲልም ግብርና ሚኒስቴር አስታውቋል።

"ኃላፊነት የተሞላበት የመሬት አሥተዳደር የአካታችና ዘላቂ ልማት ጎዳና" በሚል መሪ መልዕክት ብሔራዊ የምክክር መድረክ በመካሄድ ላይ ነው። በውይይቱ የተገኙት በግብርና ሚኒስቴር በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ ኢፋ ሙለታ፣ በአዲሱ የግብርናና መሬት ልማት ፖሊሲ መሰረት የግብርና መሬትን በዘመናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል።

መሬትን እንዴት ማልማትና ምርታማ ማድረግ እንደሚገባ በአማራና በጋምቤላ ክልሎች እየተሠራ ባለው ፕሮጀክት ጥሩ ተሞክሮ አግኝተናል ያሉት የሚኒስትሩ አማካሪ፣ የግብርና ኢንቨስትመንት ብዙ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም ኢኮኖሚውን ሊያሸጋግር የሚችል እንደሆነ አብራርተዋል።

በአዲሱ የግብርናና መሬት ልማት ፖሊሲ መሠረት የእርሻ ኢንቨስትመንት በዘመናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ገልፀው፣ መድረኩ ከውጭም ሆነ በሀገር ውስጥም ያሉትን ልምዶች ለመቀመር የሚያግዝ ነው ሲሉ አቶ ኢፋ ሙለታ ተናግረዋል።

በመድረኩ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ጥሩማር አባተ በበኩላቸው፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማትን ለመተግበር በጋራ እንሠራለን። የግብርናው ዘርፍ እንዲዘምንና በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ የግሉ ዘርፍም እንዲሳተፍበት ማበረታቻ ማቅረብ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ተቋሙ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ይዞ እየሰራ እንደሚገኝና ባለፉት ሶስት ዓመታት ያጋጠሙ ድክመቶች በመገምገም ለቀጣይ ሶስት ዓመታት ዕቅድ አውጥቶ እየሰራ እንደሆነ በመግለፅ መሬትን ውጤታማ ለማድረግ አጠቃቀም ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ነው የገለጹት።

ምክክሩ በግብርና ሚኒስቴር እና በጂ አይ ዜድ ኃላፊነት የተሞላበት የመሬት ኢንቨስትመንት አሥተዳደር ፕሮጀክቶች ትብብር የተዘጋጀ ነው። ፕሮጀክቱ በአማራና በጋምቤላ ክልሎች ከ2019 እስከ 2023 እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን በመድረኩ ተገልጿል።

የጂ አይ ዜድና የአውሮፓ ኅብረት ተወካዮች ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬትን በአግባቡ፣ በውጤታማነት በመጠቀምና በማስተዳደር ምርታማነት እንዲያድግ በጋራ መሥራታቸውን እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ከመሬት ባሻገር የሚሠራ የሰው ኃይል፣ ዕውቀት እና ተስማሚ የአየር ንብረት ያላት ናት ያሉት ተወካዮቹ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ፣ የተሻሻለውን ፖሊሲ ይበልጥ ለዘመናዊ ግብርና ጠቃሚ እንዲሆን እንጥራለን ነው ያሉት። ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገትና የግብርና ኢንቨስትመንት ውጤታማነት አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ እንደሚያደርጉም አስታውቀዋል።

# የ ‹‹አዳባ ዶዶላ›› ኢኮ- ቱሪዝም በዓለም ቱሪዝም ድርጅት ተመራጭ ሆነ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



አዲስ አበባ፡- የ‹‹አደባ አዶላ›› ኢኮ-ቱሪዝም በማደግ ላይ ከሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎች ውስጥ አንዱ በመሆን በዓለም ቱሪዝም ድርጅት ተመራጭ መንደር በመባል መመረጡን የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን አስታወቀ።

በኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የማርኬቲንግና ፕሮሞሽን ዳይሬክር አቶ አብዱ ገሊጋሎ ለበሪሳ ጋዜጣ እንደገለፁት፤ በአሁኑ ወቅት ለ‹‹አደባ አዶላ›› ኢኮ-ቱሪዝም መንደር የተሰጠው እውቅና በቀጣይ ሥፍራውን ሙሉ የቱሪስቶች መዳረሻ የማድረግ አመኔታ ተጥሎበት ነው። የሥፍራው መመረጥም ለክልሉ ቱሪዝም ማደግና ለአካባቢው ነዋሪዎችም ዘርፈ ብዙ ጠቃሜታዎች እንደሚኖሩት አስገንዝበዋል።

አካባቢውም ሰፊ የደን ሽፋን ያለው ሲሆን፤ በውስጡም የተለያዩ የዱር እንስሳትና አዕዋፍት ያሉበት፤ በተፈጥሮ ሃብቱ የታደለ እንደሆነ እና የሰዎችንም ቀልብ የሚይዝ ስለመሆኑም አብራርተዋል።

እንደ አቶ አብዱ ገለፃ፤ ስፍራው በፈረስ እና በእግር ጉዞ የሚደረግበትና የማይጠገብ መሆኑን ጠቁመው በዶዶላ በመግባት ውስጥ ለውስጥ እስከ ባሌ ብሄራዊ ፓርኮች ድረስ በፈረስ ለመጓጓዝ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶች እየተከናወኑ መሆኑን አብራርተዋል። ለቱሪስቶችም ማረፊያ እና መዝናኛ ስፍራዎችም በ20 ኪሎ ሜትር ርቀት መኖሩን ገልጸዋል።

የአዳባ ከተማ ከንቲባ አቶ ታጁ ሁሴን በበኩላቸው፤ መንደሩ በዓለም ቱሪዝም ድርጅት ተመራጭ መሆኑ እንዳስደሰታቸውና ኢኮ-ቱሪዝሙ ለአካባቢው ነዋሪዎች ከፍተኛ ፋይዳ እያስገኘ መሆኑን አመልክተዋል።

ጥብቅ ደኑ በአካባቢው ለተደራጁ በርካታ ወጣቶችም ሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከብት በማድለብ እና በንብ ማነብ ስራ ላይ የተሰማሩ ወጣቶች መኖራቸውን አስረድተዋል።

የሦስት መንደር ነዋሪዎችም ባለፉት ሁለት ዓመታት ከካርቦን ንግድ (carbon trading) ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘታቸውንም ከንቲባው ገልፀዋል።

# በሃዋሳ ከተማ የቱሪስት ፍሰቱ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል

**ኤፍሬም አንዳርጋቸው**

ሃዋሳ፡- በከተማዋ ያለው አስተማማኝ የፀጥታ ሁኔታ እና የቱሪስት መዳረሻዎች መስፋፋት የከተማዋን የቱሪስት ፍሰት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጎታል ሲል የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

ከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ስምንት ወራት ከውጭ እና ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ከ165 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ ከ158 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ያገኘ ሲሆን በዚህም የእቅዱን 88 በመቶ ማሳካት ችሏል።

የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ባህል ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ ዳርጊቱ ጫሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከስቶ የነበረው የኮሮና ወረርሽኝ እና በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች የተፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ፈጥረው ነበር።

ይሁንና የከተማ አስተዳደሩ የከተማዋን ፀጥታ የማረጋገጥ፣ ለቱሪስቶች ምቹ፣ ማራኪና ተመራጭ መዳረሻ ለማድረግ በሰራቸው የተለያዩ ሥራዎች የከተማዋን የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር አድርጎታል ብለዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ስምንት ወራት ከ62 ሺህ በላይ የውጭ አገር ጎብኚዎችን ለመሳብ አቅዶ ከ59 ሺህ በላይ ጎብኚዎችን በመሳብ የእቅዱን 84 በመቶ ማሳካት ችሏል። በተመሳሳይ ከ350 ሺህ በላይ የአገር ውስጥ ጎብኚዎችን ለመሳብ አቅዶ ከ346 ሺህ በላይ ግለሰቦች ሃዋሳ ከተማን ጎብኝተዋል። ይህም አስደዳደሩ ካቀደው ጋር ሲነፃፀር የእቅዱን 98 በመቶ መፈፀም ተችሏል ሲሉ ዳርጊቱ ጫሌ ተናግረዋል።

ከተማዋን ውብ፣ ጽዱና ለመዝናናት ምቹ ማድረግ እንዲሁም ወደ ከተማ የሚመጣ ቱሪስት እንግዳ እንዳይሆን እንግዳ ተቀባይነት መንፈስ እንዲኖር፣ የፀጥታ ችግሮችን በተለያዩ አደረጃጀቶች የመከላከል እና የመሳሰሉ ስራዎች የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር አስችሏል።

የሃዋሳ ሐይቅ የቱሪስት መዳረሻነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ሥራዎች መሰራታቸው፣ ምቹ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የሐይቅ ላይ መዝናኛ እንዲኖር መደረጉ ለቱሪስት ፍሰቱ ዕድገት ጉልህ ሚና ተጫውቷል ብለዋል።

በቱሪዝም መስክ የተገኘውን ውጤት የበለጠ ለማስፋት እና ለማጠናከር የከተማ አስተዳደሩ በ2015 ዓ.ም የጀመረው የታቦር ተራራ የማልማት ፕሮጀክት በፍጥነት እየሰራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 80 በመቶ መድረሱን የገለጹት ወይዘሮ ዳርጊቱ፤ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ እስከ መጪው ሰኔ ወር ይጠናቀቃል። ይህም ለክልሉ ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ የቱሪዝም ዕድገት የራሱን ድርሻ እንደሚያበረክት እምነታቸውን ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ የሲዳማን ባህል እና ትውፊት እንዲያሳይ፣ ክልሉ የሄደበትን የትግል ምዕራፍ ለመግለጽ ወደ ተራራው መውጫ እና መውረጃ 130 ደረጃዎች ያሉት ሲሆን ለሰርግ ፣ ለልደት፣ እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ለመዝናኛነት ያገለግላል ሲሉ ተናግረዋል።

በከተማ የሰፈነው ሰላም፤ የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር በርካታ ክልላዊ፣ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ኹነቶች እንዲካሄዱ አስችሏል። በቀጣይ ከተማዋ የኮንፈረንስ ከተማ እንድትሆን በስፋት ይሰራል ሲሉ መምሪያ ኃላፊዋ አስታውቀዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ትልቁ ራዕይ ከተማዋን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ማድረግ ሲሆን ከዚህ ቀደም ከነበሩት የቱሪዝም ሀብቶች በተጨማሪም ሌሎች ከተማዋን የበለጠ ሊያሳድጉና ሊያስተዋውቁ የሚችሉ መዳረሻዎች እየተሰሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

# “ረመዷንን ስንፆም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ይኖርበታል፡፡ ከአምስቱ የእስልምና መሰረቶች አንዱየሆነው የረመዷን ፆምን ስንፆም ካላስፈላጊ ድርጊቶች እራስን በመቆጠብ፣ በሰላም ፣ በፍቅር ፣ በይቅርታ ማሳለፍ ይኖርብናል ያሉት ሼህ ሃጂ ኢብራሂም፤ ሕዝበ ሙስሊሙ በድርቅ እና

በጦርነት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን ወገኖች በማገዝ የፆሙን ወቅት ማሳለፍ አለበት ነው ያሉት ።

በረመዷን ፆም ሙስሊሙ ህብረተሰብ እንደወትሮ ሁሉ ሀገራዊ ሠላምና ልማትን በሚያመጡ ጉዳዮችም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ምክር ቤቱ ጥሪውን አስተላልፏል።

ምክር ቤቱ ለመላው ዓለም ሙስሊም ሕብረተሰብ በሙሉ ፆሙ የጤና፣ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን መልካም ምኞቱን አስተላልፏል።

የ 1444ኛውን የረመዷን ፆም ነገ እንደሚጀመር ታውቋል።



ፎቶ ፡- አሸናፊ ጉደታ

# የኢትዮጵያ ታምርት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሚሰራበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህም እንደ ጃፓን፣ ሲንጋፖር፣ ማሌዥያ መሰል በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከተሳካላቸው አገራት ተሞክሮዎችን በመውሰድ ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር የተጀመረ ንቅናቄ መሆኑን አስታውሰዋል።

ሀገራዊ ንቅናቄው የተጀመረው የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትን ለማሳደግና ኢንቨስትመንቱን ለማስፋፋት መሆኑን ገልጸው፤ የንቅናቄው ዓላማዎችም የኢንዱስትሪ ባህልን ማስረፅ፣ የምርቶችን ጥራት፣ አይነት እና ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን መጨመር እና ተኪ ምርቶች የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ማበረታታት መሆኑን አመልክተዋል። እነዚህን ዓላማዎች ከማሳካት አኳያም በተሰሩ ስራዎች ውጤታማ ጅምሮች መታየታቸውን ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የስራ ማስኬጃ ብድር በማጣት፣ የመሬትና የግብዓት አቅርቦትና በተለያዩ አስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት ስራ አቁመው የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ወደ ማምረት ስራቸው እንዲገቡ ተደርጓል። ይህን ጅምር ውጤት ለማስቀጠልም ደረጃውን የጠበቀ ሀገር አቀፍ ኤክስፖ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እና የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር ዶክተር ዓለሙ ስሜ፤ የኢትዮጵያ ታምርት 2023 ሎጎን ይፋ አድርገዋል። በኤክስፖው 350 ድርጅቶች ምርታቸውን በማሳየት ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በኤክስፖው አጋር ኢንዱስትሪዎች፣ ላኪዎች፣ የንግድ ማህበራት፣ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የመንግሥት ኤጀንሲዎች ይገኙበታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሚያዚያ 29 ቀን 2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታምርት ሀገራዊ ንቅናቄን በአገር አቀፍ ደረጃ በይፋ ማስጀመራቸው ይታወቃል።

# “መንግሥት በአሜሪካ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በተዘጋጀችበት ወቅት ላይ የወጣ በመሆኑ መግለጫው ወቅቱን ያልጠበቀ ነው ብሎታል።

በተጨማሪም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ይህን መግለጫ ለማውጣት ያሰበበት ዓላማ ምንም ይሁን ምን መግለጫው በሀገሪቱ አንድን ወገን በሌላኛው ላይ ለማነሣሣት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ቆስቋሽ መግለጫ ነው ብሏል፤ የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመግለጫው።

ወገንተኛ እና ከፋፋይ የሆነው ይህ የአሜሪካ አካሄድ ሀገሪቱ በኢትዮጵያ አካታች የሰላም ሂደት እንዲረጋገጥ ስታደርገው የቆየችውን ድጋፍ የሚያጨናግፍ ነው ብሏል። የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ጉብኝት ሁለቱ ሀገራት ግንኙነታቸውን ይበልጥ እንደሚያጠናክሩ ተስፋን የፈነጠቀ ነው ያለው መግለጫው፤ በጉብኝቱ ወቅት የተደረገው ግልጽ ውይይት እና የተደረሰበት መግባባት የሁለቱን ሀገራት ስትራቴጂያዊ አጋርነት ለማስቀጠል ይረዳል ብላ ኢትዮጵያ እንደምታምን ገልጿል።

በሽግግር ፍትሕ ላይ ሀገራዊ ምክክር በማካሄድ መግባባት መፍጠርን ጨምሮ ለተበዳዮች ፍትሕን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የተጠያቂነት ርምጃዎች እንደሚወሰዱ ያረጋገጠው መግለጫው፤ የኢትዮጵያ ወዳጆችም ገንቢ ድጋፍ በመለገስ ይህን ሂደት እንዲያግዙ ጥሪ መቅረቡ ተገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት መግለጫ የኢትዮጵያን የሰላም ጥረት ያላገናዘበና ተቀባይነት የሌለው ነው!

በሰሜናዊ የሀገራችን ክፍል ለሁለት ዓመት የቆየው ጦርነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ተቋጭቷል። ጦርነቱ ሀገርና ሕዝብን ለከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጥፋት ዳርጓል። ጥሎት ያለፈው ጠባሳም በአግባቡ ያላገገመ፤ ለማገገምም ጊዜ የሚፈልግ እንደሆነም ይታመናል።

ጦርነቱ ከተቀሰቀሰበት ወቅት ጀምሮ ከጦርነቱ ለማትረፍ ብዙ አካላት ራሳቸውን/ እጃቸውን አስገብተዋል። የአንድን ቡድን ፍላጎትና ዓላማ ታሳቢ ያደረጉ ፍትሃዊነት የጎደላቸው እና ወገንተኝነት የተላበሱ ተግባራት በአደባባይ ሲከወኑ እና ሲደመጡ ተስተውለዋል።

መንግስት ችግሩን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት ያደረጋቸውን ጥረቶች የሚገዳደሩ የአንድን ቡድን አሸናፊነት የሚናፍቁ፣ ለዚህም የተገዙ ያልተገቡ ተግባራት በተለይም ከአንዳንድ ሀገራትና ከመገናኛ ብዙኀኖቻቸው በስፋት ታይተዋል።

እነዚህ ሀገራትና መገናኛ ብዙኀኖቻቸው ሀገርን ከጥፋት የመታደግ የህግና የሞራል ኃላፊነት ያለበት የኢትዮጵያ መንግስት ፤ ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት ያደረጋቸውን ጥረቶች ያልተገባ ትርጉም ከመስጠት ጀምሮ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሳሳተ ትርጉም እንዲይዙ በተናበበና በተቀናጀ መንገድ ተንቀሳቅሰዋል።

መንግስት ከጦርነቱ አትራፊ ሊሆኑ የሚችሉት ለሀገሪቱ በጎ የማያስቡ ኃይሎችና ቡድኖች ናቸው በሚል፤ በአንድ በኩል በኃይል ሕዝብን ለማንበርከክ የተደረገውን ጥረት በኃይል እየመከተ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለዘላቂ ሰላም ቁጭ ብሎ መወያየትን ግብ አድርጎ በሀገሪቱ በድርድር ላይ የተመሰረተ ሰላም እንዲሰፍን አድርጓል።

ከዚህም ባለፈ በጦርነቱ ለተጎዱ አካባቢዎች አስፈላጊ የሆኑ ሰብዓዊ ርዳታዎች እንዲቀርቡ እያደረገ ነው፤ አስፈላጊ የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች እንዲሟሉም በከፍተኛ ቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። አብዛኞቹ የግጭት አካባቢዎች ወደ ቀደመው ሕይወት እንዲመለሱም በትኩረት እየሰራ ነው።

መንግስት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተደረሰ ስምምነት መሰረት፤ ከሕወሓት ጋር ተቀራርቦ በመስራት ስምምነቱ መሬት እንዲወርድ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ነው። በዚህም ተስፋ ሰጭ ሂደቶች ስለመኖራቸው በየዕለቱ /ከመንግስትና ከሕወሓት/ የሚደመጡ መረጃዎች የሚያመላክቱት እውነታ ነው።

ከዚህም ባለፈ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የሚያስችል የሽግግር ፍትሕ እውን ለማድረግ ፖሊሲ አማራጮችን በመለየት ብሔራዊ ምክክር ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነው። ይህ ደግሞ ለመላው ሕዝባችን ትልቅ ትርጉም ያለውና በተስፋ የሚጠብቀው ጉዳይ ነው።

ይህ እየሆነ ባለበት ወሳኝ ወቅት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ጦርነት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተከስቷል ሲል የደረሰበትን ድምዳሜ በኢትዮጵያ መንግሥትም ሆነ ሕዝብ ዘንድ በፍፁም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይደለም። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና የተመድ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር በጋራ ካደረጉት ምርመራ እና ከደረሱበት ምርመራ አንፃር ሲታይም ደምዳሜው ስህተት መሆኑ የሚያሳይ ነው።

የመስሪያ ቤቱ በመግለጫ ያወጣው ያልተገባ ድምዳሜ ኢትዮጵያውያን ችግሮቻችውን በራሳቸው አቅም መፍታት እንደሚችሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስመሰከሩበትን ትልቅ ክስተት /አጋጣሚ ያላገናዘበና በሀገሪቱ ዘላቂ እርቅና ሰላም ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት ከበሬታ የሌለው ነው።

ኢፍትሃዊነት የተንጸባረቀበት፣ ይህ የአሜሪካ አካሄድ ሀገሪቱ በኢትዮጵያ አካታች የሰላም ሂደት እንዲረጋገጥ ስታደርገው የቆየችውን ድጋፍ የሚጻረር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ከአሜሪካ መንግስትና ሕዝብ ጋር ያለውን ወዳጅነት የሚሸረሽር ጭምር ነው።

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉብኝት ተከትሎ ፤ ተስፋ የተደረገበትን የሁለቱን ሀገራት የግንኙነት መሻሻል መልሶ ጥያቄ ውስጥ የሚጨምር ነው።

ኢትዮጵያውያን ዛሬም ቢሆን በሀገሪቱ ብሔራዊ እርቅ ፤ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን ለሚያደርጉት ጥረት የአሜሪካ መንግስት እና ሕዝብ ሁነኛ አጋር እንደሚሆን ከፍ ያለ አመኔታ አላቸው። ከአንቶኒ ብሊንከን ጋር በአዲስ አበባ የተደረጉ ግልጽ ውይይቶች እና የተደረሰባቸው መግባባቶችም ሁለቱን ሀገራት ስትራቴጂያዊ አጋርነት ለማስቀጠል እንደሚረዳም ይታመናሉ! ወዳጅነቱና ግንኙነቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም የአሜሪካ መንግስት ኢፍትሃዊ ከሆኑና ተቀባይነት ከሌላቸው ርምጃዎችን ራሱን ማቀብ ይኖርበታል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## «የመደመር ትውልድ» መጽሐፉ ላይ ዳሰሳ ያደረጉ የስነጽሑፍ ባለሙያዎችና ምሁራን ምልከታ

"የመደመር ትውልድ" በሚል ርዕስ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተጻፈው መጽሐፍ ማስተዋወቂያ መድረክ ላይ በመጽሐፉ ላይ ዳሰሳ ያደረጉ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎችና ምሁራን ሀሳባቸውን አጋርተዋል።በዕለቱ ከቀረቡት አስተያየቶች ለዛሬ የአርቲስት ደበበ እሸቱ "ወግ አጥባቂ" በሚል የቀረበው እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

### ወግ አጥባቂ

ማነፃፀሪያ የሌለው ትውልድ ዘመኑ ባካኝ ነው። የእውነት፣ የዕውቀት፣ የፈጠራ፣ የፍልስፍና የብልፅግና፣ የልዕልና፣ የሕልውናው ኃያልነት ግርማ ሞገሱ፣ ትዝታው፣ ተስፋው ሁሉ ከመፃህፍት ጋር የተቆራኘ ነው።

ዛሬ የሚመረቀውን "የመደመር ትውልድ" በሚል ርዕስ ያቀረቡልንን ክቡር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን በቅድሚያ አመሰግናለሁ። መጽሐፉን ካገኘሁበት እለት አንስቶ ሳነበው ትምህርት ቤት ያለሁ እስኪመስለኝ ድረስ ነበር ኃይሉ። የእኔ ማንነት ከመሰረቱ፣ በሰብዓና ተገንብቶ ነው ዛሬ ላይ የቆመው። ባጭሩ እኔ የመነሻዬ ውጤት ነኝ።

ወግ አጥባቂ ማለት ምን ማለት ነው? ወግ አጥባቂስ ማን? ምንድን ነው? በተፈጥሮ፣ በባህል፣ በእምነት፣ በእውቀት፣ በተፈለገው አቅጣጫ ብንወስደው ምን ማለት ለሚለው፣ ቀጥተኛነት፣ ወይንም እውነተኛነት/ ምን? ለሚለው ሰው መሆንና/ ምንድን ነው ለሚለው ደግሞ ሰውኛ ባሕሪያት ብለን ልንጠቀልለው ያስችለናል።

ዛሬ በሚመረቀው የክቡር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ፣ 3ተኛ መጽሐፍ ላይ ከገፅ 35 አንስቶ እስከ 39 ድረስ በአግባቡና የጎደለ ነገር ሳይታከልበት ተሰድሮ የቀረበ ስለሆነ፣ አላስፈላጊ ፀጉር ስንጠቃ ውስጥ መግባት አያስፈልገኝም። የኔን እንደ መንደርደሪያ በመውሰድ የተጠቀሱትን ገፆች በማንበብ በቂ ትምህርታዊ ትንታኔ ይገኛል ብዬ አምናለሁ። ማስረጃ ይሆነን ዘንድ ከወግ አጥባቂነት የሚፈረጁ ድንቅ ለኢትዮጵያ ለውጥ አምጪ ሰውኛ የሀገር ምሰሶዎችን እንዳነሳ ይፈቀድልኝ።

### አፄ ቴዎድሮስ

በቆራጥነትና ኢትዮጵያን አትንኩ ባይነት ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግና ሕዝቡንም ለሥራ ተነሳሽነት ፍላጎት እንዲያድርበት በማነሳሳት ሙከራቸው ወደ ሀገር የገቡ ነጮችን ለሀገር መጠበቂያ የጦር መሳሪያ ለማሰራት ብልሃታቸው... ።

### እምዬ ምኒልክ

በሰው አክባሪነትና በሰውነት አስቀዳሚነት። ለኢትዮጵያ ዕድገት በማሰብ የእህል ወፍጮ፣ ስልክ፣ መኪና፣ ት/ቤት፣ የውሃ ቧንቧ፣ ባቡር፣ የባህር ዛፍ፣ ሲኒማ እና ሌሎችም ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ነገሮችን በማስገባታቸው።

### ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ

የደጋግ አያት የምሽት ምርቃት ያልራቃቸው በመሆናቸው በምኒልክ የተጀመረውን አዲዲስ በረከት በማስቀጠል ላይ የበኩላቸውን ማድረጋቸው፣ በተለይም የውጭ ቋንቋዎችን የሚያስተምሩ ኢትዮጵያዊያን አነስተኛ በመሆናቸው በራሳቸው ገንዘብ ያስገነቡትን የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትን ከካናዳ መንግሥት ጋር በመነጋገር ካናዳዊያን መምህራን እንዲመሩት ማድረጋቸው፣ በእንግሊዛዊው ጄኔራል ዊንጌት ስም የተቋቋመውን ት/ቤትም እንግሊዞች እንዲያስተዳድሩት በስምምነት በማድረጋቸው፣ የኢትዮጵያን አየር ኃይልንም እንዲሁ ማሰልጠኑን ስዊድኖች እንዲመሩት ማድረጋቸው፣ ለትምህርቱ ዘርፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝቷል።

ለዩኒቨርሲቲነት ተገቢ የሆነ ግንባታ ወቅቱ ይጠይቅ ስለነበር የራሳቸው መንግሥት ሲገለገልበት የነበረውን በሰፊ ቦታ ላይ የተመሰረተውን ሙሉ ህንፃውን ለዩኒቨርሲቲው በመስጠታቸው ዓለምና ሀገሬ በዕውቀት እንዲተሳሰሩ የሚተጉ አልነበሩም።

የኢጣልያ ፋሽስት ኢትዮጵያን በግፍ ቅኝ ግዛት ሊያስተዳድር በቋመጠ ጊዜ በስደት ወደ እንግሊዝ ሃገር ሄደው፤ ከካቶሊኩ ቄስ አቡነ ጃርሶ ጋር በመምከር ኢትዮጵያ በወቅቱ በነበረው ሊግ ኦፍ ኔሽን እንደ መሥራች አባልነቷ ሊደረግላት የሚገባውን የአባል ሀገራት ጥበቃ በአግባቡ እንዳልተተገበረላት በማሳወቅና ታሪካዊ ንግግር ማድረግ በመቻላቸው ታሪክ መርጦ ብቻ ሳይሆን ፈቅዶ በብራና ላይ የክብርና የሞገስ ስማቸውን በመጻፍ ፣ ከጥቁሮች ፊት ያሉ ታላቅ የዲፕሎማሲ አውራ ሲል ይዘምራል።

ከሁሉም በላይ የአፍሪካ አንድነት እንዲመሰረት ፅኑ ፍላጎታቸው ስለነበር "ዛሬ አንድነታችንን በፊርማችን ሳናፀድቅ ከዚህ አዳራሽ አንወጣም" ብለውና ሁሉንም አግባብተው የአንድነት ማእከሉም በሀገራችን እንዲሆን በማድረጋቸው ሊመሰገኑ ይገባል።

### ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን

ሁሌም እንደምለው ጥቂቶች እኩያ የላቸውም። የግብርም ሆነ የፍቅርም ርቀትን ብቻቸውን ይቆሙበታል። ይከብሩበታል። ጋሽ ጸጋዬም ስለኢትዮጵያዊነት በተለያዩ ግጥሞቹ ከማቀንቀኑም ባሻገር፣ በተውኔቶቹም ብሶቱን፣ መንተክተኩን፣ ብሎም የሚፋጅ ተቃውሞውን በዘዴ የማስተላለፍ ተግባራትን ለማሳየት መድፈሩ ከፍተኛ ነበር። የንጉሱ ሥርአት እንደሰለቸውና ለውጥ እንደሚፈልግ ያሳየበት የከርሞ ሰው ሊጠቀስ ይችላል።

ደርዘ ሙሉ ብዕሩ ትኩሳቱ ከባድ ነበረ። የሚቀበጅ ሥርዓት፣ የቀረደደ አስተዳደር አጭር ለሊት እንጂ ለረጅም መዓልት እንደማይበቃ በሰም እና ወርቅ ነግሮናል። መክሮናል። ሌሎችንም ድርሰቶቹን በሳንሱር አከርካሪ እንዳይታነቁበት ትርጉም፣ አዛማች ትርጓሜ እያለ ዘመንን ጥሶ እንዲፈከርበት፣ እንዲዘመርበት ጉልበታም ባለቅኔ ነበረ። ለጠሊቅና ረቂቅ ሃሳቡ ይኸው ስሙን ሳነሳው አምስት የሰውኛ ህዋሳቶቼ ነፍሴን እየኮረኮሩ አንድ ነገር ጨምረው ሲደሰቱ ይታወቀኛል።

### አብዬ መንግሥቱ ለማ

ነገርን በጨዋታ በማሸነፍ፣ የሀገራቸው ተቆርቋሪ፣ በድርሰቶቻቸውና በግጥሞቻቸው በጥቁሮች ላይ የደረሰውንና በመድረስ ላይ ያለውን ግፍና በደል ሞጋችነታቸው እንደ ማስረጃ ባሻ አሸብር በአሜሪካ ግጥማቸው ጥሩ ምሳሌ ነው።

ጋሽ መንግስቱ በእንግሊዝ ሀገር በኤምባሲው ውስጥ ይሰሩ በነበረበት ወቅት የእንግሊዝ ፖርላማ ሲካሄድ እንዲመለከቱ ፍቃድ ነበራቸው። ከእለታት በአንዱ የስብሰባ ወቅት ገብተው ሥርአቱን ይከታተሉ በነበረበት ወቅት አንድ ሕዝባዊ የሆነ ጉዳይ ተነስቶ ሕዝቡን የማይጠቅም ውሳኔ ሊያልፍ ሲል፣ ጎረምሳው መንግሥቱ ለማ በድንገት ብድግ ብለው ኦርደር! ኦርደር! ብለው በመጮኻቸው ሂደቱ ተቋርጦ እሳቸውም በፖሊስ ታግተው ወጥተው ጉዳዩ ለኢትዮጵያ አምባሳደር ተነግሮ መንግስቱ ለማም ከለንደን ተነስተው ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ሌላ ሀገር እንዲመደቡ ተደርጓል።

### ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም

ለእውነት በመቆም፣ ሰው በሌለበት፣ በክፉም በደግም ስሙ እንዲነሳ ባለመፈለግ፣ ስለ ሀገር እድገት፣ ሰብዓዊነት፣ ስለፍትህ በመቆማቸው፣ በኢትዮጵያዊነት ጥንካሬያቸው፣ ለቆሙለት ዓላማ ዝንፍ የማይሉ በመሆናቸው። በርካታ መፅሐፎቻቸው ለኢትዮጵያ ተብለው ሳይሆን መላ አፍሪካ እንዲገለገልባቸው የተዘጋጁ በመሆናቸው እነ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ተሽቀዳድመው አሳትመዋቸዋል።

የፕሮፌሰር መስፍን ቤት ሁልጊዜም ከሳቸው ለመማር ለሚሹ ወጣቶች ክፍት በመሆኑ እያንዳንዱ ቀናት ፕሮግራም ተይዞላቸው ወጣቶች ከጋሽ መስፍን በሚያገኙት እውቀት ተጠቃሚ ሆነው ቀኑን ሳይረሱ ሰዓቱን አክብረው ጥያቄዎቻቸውን በወጉ በቅደም ተከተል አስፍረው መጥተው የሚጀመርበት ሰዓት እንጂ የሚያልቅበት ሰዓት ሳይወሰን ይቀጥል ነበር። በዚህም ነው የቀብራቸው እለት ወጣቶቹ ከያዙት ባነር ላይ "መምህራችን ዛሬ አረፉ፣ እኛ ግን ባዷችንን ቀረን" ብለው የተሰናበቷቸው።

### እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ

ቀጠሮን በደቂቃም ባለማሳለፍ፣ የቀጠራቸውን ሰው አሁን ያንተ ሰዓት ስንት ይላል ብለው ጠይቀው ሰዓታቸውን በማስተካከል ቀጠሮውንም ሰዓቱንም በማክበር ባህላቸው አድርገውት ኖረዋል፣ ዓላማቸውን የማይደራደሩበት፣ በጥበባዊው የሥዕል ሥራቸው መብታቸውንና ራሳቸውን ያስከበሩ በመሆናቸው። በጥቂቱ ከሚጠቀሱት ወግ አጥባቂዎች የዘመናችን ኢትዮጵያ ብርቅዬዎች ናቸው።

የዓለም ሎሬት አፈወርቅ በአንድ ሆስፒታል ውስጥ ሥዕል እንዲስሉ በንጉሡ ተጠይቀው በመስራት ላይ ሳሉ አንድ ባለስልጣን ስዕሉ ከምን እንደደረሰ ለማየት መጥተው ከተመለከቱ በኋላ ስለ ስዕሉ አቃቂር በማውጣታቸው፣ ሰዓሊው የያኔዬው ወጣት አፈወርቅ ከሚሰራበት በመሰላል ወርዶ ለባለስልጣኑ ብሩሹንና የቀለም መደባለቂያውን ይሄው እስቲ ስህተቱን ያርሙልኝ ብሎ ግቢውን ጥሎ በመውጣት አስደንግጧቸው በእኚሁ ባለስልጣን ተለምኖ ሥራውን መቀጠሉ ለብዙዎች ትምህርት መሆኑና እራሱን ማስከበሩ ይነገርለታል።

እናም እነዚህ ወግ አጥባቂ ኢትዮጵያዊያን፣ ዛሬም ድረስ ለኢትዮጵያችን መከበሪያና እዚህ መድረስ የየራሳቸውን አሻራ በማስቀመጣቸው፣ ከዚህ ዓለም በሥጋ ቢሸኙም ትሩፋታቸው በቁም ላለነው መነሻዎች ናቸው። ወግ አጥባቂነት በሁሉም አቅጣጫ፣ ቀጥተኛነትና ሥርዓት ያለው አመራር፣ ሥርዓት ያለው ተመሪን ማፍራት ያስችላል። የቀረደደ ሃሳብና ምንግግ ብለው ክቡር ነገር ጽዩፍ የሆኑ፣ እኩይና እራስ ወዳድ አደራ በላዎች፣ ተለክቶ የተሰጣቸውን ተግባራዊ ሳያደርጉ፣ በይጨመርልኝ በሽታ የተለከፉና ከሀገር በላይ ራሳቸውን የሚያስቀድሙ ስግብግቦች ኢትዮጵያችንን አጥለቅልቀዋት የትውልድ ብካይ ሆነን እንዳንኖር ስጋት አለኝ።

ማነፃፀሪያ የሌለው ትውልድ ዘመኑ ባካኝ ነው። የእውነት የእውቀት፣ የፈጠራ፣ የፍልስፍና፣ የብልፅግና የልእልና፣ የሕልውናው ኃያልነት፣ ግርማ ሞገሱ፣ ትዝታው፣ ተስፋው ሁሉ ከመፃሕፍት ጋር የተቆራኘ ነው። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ እኔ ለእኔ አቀረብኩለት፣ እኚህ ሰው መቼ ነው መጽሐፍ ለመፃፍ ጊዜ የሚያገኙት? ቀኑ ሁሉ የፈተና፣ የአቤቱታ፣ የልማት፣ ዙሪያቸው በተለያየ የአዲስ አበባ፣ የድሬዳዋና የሌሎችም ክልሎች ጥያቄ የሚቀርበው ለእሳቸው ሆኖ ምን ጊዜ ተርፏቸው ነው መፅሐፍ የሚፅፉት? ይህን እሳቸው፣ እንቅልፍ አልባው ደራሲ ብቻ ናቸው መመለስ የሚችሉትና፣ በድጋሚ ለብርታት ጥንካሬያቸው ለደራሲው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ምስጋናዬ ይድረስልኝ። እናንተም ስላዳመጣችሁኝ ምስጋናዬ የበዛ ነው! አመሰግናለሁ!

## ተጠየቅ

# «አብዛኛዎቹ ኢንተርፕራይዞች እየሰሩ ያሉት ከማምረት አቅማቸው ሀምሳ በመቶ ብቻ ነው‹»

- አቶ ጳውሎስ በርጋ
የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር

አስመረት ብስራት

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት «የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት» አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ በቅርቡ አውጥቷል። ደንቡ የኢንተርፕራይዝ ልማቱን ስልጣንና ተግባር በዘረዘረበት አንቀጽ ልማቱ ኢንተርፕራይዞች እርስ በእርስና ከከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ከሌሎች ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በግብአት፣ በገበያና በቴክኖሎጂ የሚተሳሰሩበትን ስልቶች እንደሚቀይስና ተግባራዊ እንደሚያደርግ አስቀምጧል። ይህ ተቋም የስራ እድል በመፍጠር ረገድ ከፍ ያለ ድርሻ እንዳለውና ተኪ ምርቶችን በማምረትም ሚናው የጎላ መሆኑ ይታመናል። የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ጳውሎስ በርጋ በ"ተጠየቅ "አምዳችን እንግዳ በማድረግ በተቋሙ እየተሰሩ ያሉትንና ሊሰሩ የታቀዱትን ስራዎች አስመልክተን ቆይታ አድርገናል።**



መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**አቶ ጳውሎስ፡-** የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በቅርቡ በአዲስ ደንብ በደንብ ቁጥር 526/2015 ተቋቁሟል። ከአዲሱ ደንብ በኋላ መዋቅር ተጠንቶ ሊፀድቅ ዝግጅት ላይ ነው። በአሁኑ ወቅት ተቋሙ ቀደም ሲል ከነበረው አቅም በላይ እንዲያስፈፅማቸው የተለያዩ ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል።

ከተሰጡት ኃላፊነቶች መካከል ክላስተር ግንባታ፣ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ ወደውጭ የሚላኩ ምርቶች፣ ተኪ ምርት መከታተልና ክልሎችን የመደገፍ ተጠቃሾች ናቸው። ይህ ቀደም ሲል በነበረው የተቋሙ አቅም ያልነበረና አዲስ አሰራሮችን የሚፈጥር ነው። ተቋሙ አሁን በተጨመረው አዳዲስ አቅሞች በመታገዝ አዳዲስ አሰራሮችን በመስራት ላይ ይገኛል። የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታ በጀርመን መንግስት ድጋፍ እየተጠና ይገኛል።

ተቋሙ፣ እስካሁን አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ በርካታ ስራዎችን ሲሰራ የቆየ ሲሆን፣ በተለይም የማምረቻ ማዕከላትን የመገንባት፣ የማስተዳደር እና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ስራዎችን እንዲሰጥ ተጨማሪ ተልዕኮ ተሰጥቶታል፤ በመሆኑም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ፍኖተ ካርታው ትልቅ አቅም ይሆነዋል።

ፍኖተ ካርታው ዘርፉን በውጤታማነት ለመምራትና ከጊዜው ጋር የተጣጣመ ድጋፍ ለማድረግ ምቹ የሆኑ አሠራሮችን፣ የችግር መፍቻ መንገዶችን እና ውጤታማ ቅንጅታዊ አካሄዶችን ለማሟላት እንዲቻል በዘርፉ ተሞክሮ ባላቸው የአገር ውስጥና የውጪ አገር ባለሙያዎች እየተዘጋጀ ነው።በመሆኑም ወደ ተግባር ከመገባቱ በፊት በተለይ የፌዴራል ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ አጋር አካላትና መሠል ባለድርሻዎች አስተያየታቸውን እንዲሠጡበት የተለያዩ መድረኮችም ተዘጋጅተው ነበር።

የዘርፉ ልማት የሚፈልገውን የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ፣ የማምረቻ ቦታ፣ የስልጠና፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የገበያ ትስስር እና መሰል ድጋፎችን በተገቢው ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ እንዲቻል የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ትብብር አስፈላጊ ነው። ይህ እንዲሆንም ተቋሙ ቀጣይነት ያለው የምክክር መድረኮችን ለማመቻቸት የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋት በትኩረት እየሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በራሱና ከሌሎች ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ የሚያከናወናቸውን ስራዎች ቢያብራሩልን?**

**አቶ ጳውሎስ፡-**ተቋሙ በራሱ የሚያከናውናቸውና ከሌሎች አካላት ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራቸው በርካታ ስራዎች አሉት። ለአብነት ያህል ኤሌክትሪክ ሲፈለግ ከመብራት ኃይል ጋር እንዲሁም መሬት ሲፈለግ ከመሬት አስተዳደርና ሌሎች ስራዎችንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል። በአጠቃላይ ግን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በዋናነት የሚሰራው የአቅም ግንባታ ስራዎችን ነው። በሁሉም ክልል ያሉ አነስተኛና መካከለኛ ተቋማትን የሚደገፉትን የማብቃት ስራን ይሰራል። በተቋሙ የተለያዩ የተግባር ስልጠናዎች ወጣቶች እንዲያገኙ በማድረግ ልማት ባንክ ከሚያመቻቸው የብድር ፕሮግራም ጋር ያስተሳስራል።

**አሁን ያለው የኢኮኖሚ ስርአት ገበያ መር ቢሆንም ገና ስራ ጀምረው ወደ ምርት ያልገቡ አነስተኛ አምራቾች ግን ድጋፍ ካልተደረገላቸው ተወዳዳሪነታቸው ቀርቶ ከገበያ ሲወጡ ይችላሉ**

ሌላው የተለያዩ ለዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ ጥናቶች በማስጠናት ለመንግስት የፖሊስ አቅጣጫ የማሳየት ስራ ይሰራል። ለምሳሌ የማሽነሪ ሊዝ በመንግስት ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራበት የሆነው ተቋሙ ባስጠናው ጥናት ነው። የዓለም ባንክ የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ የጀመረውም ይህ የስራ እድል ፈጠራ ስራ በተለመደው መንገድ ሊካሄድ እንደማይችል በተጠና ጥናት ነው። በዚህም የዓለም ባንክ በመጀመሪያ 276 ሚሊዮን ዶላር አሁን ደግሞ 200 ሚሊዮን ዶላር ከአገሪቱ መንግስት ጋር ተፈራርሞ ለኢንተርፕራይዞች እንዲከፋፈል የተደረገውም በጥናት ነው።

የኛ ተቋም ስራውን በመምራት ከላይ የጠቀስኳቸውን ስራዎች ይሰራል። አሁን አዲስ የተሰጠው ኃላፊነት ክላስተር ግንባታ /መሠረተ ልማት የተሟላለት የሥራ ቦታ ማዘጋጀት/ ነው። በዚህም ግንባታው በተቋሙ ተሰርቶ ለግል አልሚ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ። ተቋሙ በሚያከናውነው ተግባር ማነቆዎች የሆኑበት በአብዛኛው ቢሮክራሲ ሲሆን፣ ይህም ከአገልግሎት ሰጪዎች ቅንነት ማጣት የተነሳ የሚከሰቱ ችግሮች ናቸው። የአገር ውስጥ ግዢ ከሚያደርጋቸው ግዢ በአገር ምርት ሊተኩ የሚችሉትን ለጥቃቅንና አነስተኛ ክፍት ቢያደርግ ተቋማቱን ማሳደግ የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከመነሻው አነስተኛና ጥቃቅን ተብሎ ሲቋቋም ስራ አጥ ዜጎች ከትንሽ ደረጃ ተነስተው እስከ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ አላማ አድርጎ ነው። ነገር ግን ሁሉንም ኢንተርፕራይዞች በእኩል መጠን የገበያ ትስስር አለመፍጠር፤ የተለያዩ ድጋፎችም ለአንዱ በከፍተኛ ሁኔታ ለአንዳንዱ ለይምሰል ሲደረግ ይታያል፤ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ጳውሎስ፡-** እንደ አገር ከጥቃቅን ጀምሮ መካከለኛ ከፍተኛ ተብሎ ሲቋቋም ስራ አጥ ወጣቶችን ወደ ባለሀብትነት ለመቀየር ታስቦ ነው። ስራው ሲጀመር እያንዳንዱ ስራ ፈጣሪ ይሆንና በውስጡ ከፍተኛ ፍላጎት ኖሮት ወደ ስራ የሚገባ አለ። ሌሎች ደግሞ ስራ አጥ ተብለው የተደራጁ ወጣቶች አሉ። ሌላው በራሱ ገንዘብ ኖሮት በትንሽ ድጋፍ ከመካከለኛ የጀመረም አለ። ስኬታቸውም ሆነ ውድቀታቸው እንደየ ስራ አጀማራቸው እና ጥንካሬያቸው ይወሰናል።

በኢንዱስትሪው ሁኔታ ግን ከታች በርካታ ስራ አጦችን የያዘ ጥቃቅን ሲኖር መሀል ላይ አነስተኛ ጥቂት ቁጥር ይይዛል። ከፍተኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ዘርፍም ይከተላል። ይህ በየትኛውም አገር የተለመደ የፒራሚድ ቅርፀ ያለው አይነት አካሄድ ነው። ይህ የሆነው የመክሰም መጠኑ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የእውቀት ማነስ፣ የቢሮክራሲው ማነቆነት እና የእርስ በእርስ ግንኙነት ነው። በአብዛኛው ግን ከተደራጁት ይልቅ ስራ ፈጣሪዎቹ እንቅፋቶችን ተቋቁሞ በማለፍ በተለያዩ አጋጣሚዎች እውቀታቸውን በማሳደግ ችግሮችን በመጋፈጥ ወደ ላይ ይወጣሉ።

እንደ አገር ጥቃቅን ላይ የተደራጁ እንደ ህፃናት ልጅ እንክብካቤ የሚፈልጉ ወጣቶች አሉ። እነርሱ በቀላሉ ተስፋ ቆርጠው ስራውን እንዳያቆሙ በተቻለ መጠን ስልጠናንና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለመስራት ጥረት ይደረጋል። በአብዛኛው ግን እውቀት ሳይኖር ብሩን ለማግኘት ብቻ የሚደራጁት ይከስማሉ።

ሌላው ጥቃቅንና አነስተኛ ላይ የሚሰሩት በእድገታቸው ልክ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ሲያድጉ ግብር ከፋይ ይሆናሉ። ስለዚህ ማደግን አይፈልጉም። በማደጋቸው ቀደም ሲል የሚያገኙትን ለስኬታቸው አጋዥ የሆነውን ጥቅም ማጣት አይፈልጉም። ከግብር ከፋይነት በላይም ሲያድጉ የመስሪያ ሼዱን ስለሚለቁ ከማደግ ይልቅ አለማደጋቸውን ምርጫ አድርገዋል።

ሆኖም ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት ተቋሙ የበኩሉን ጥረት እያደረገ ሲሆን፣ አሁን የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በመጀመሪያ ስልጠና በመስጠት በቂ እውቀት ይዘው ከፍ እንዲሉና ጠንካራ የስራ ፈጣሪነት ስነ ልቦና እንዲኖራቸው አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- በዘርፉ ያሉ ተግዳሮቶችን ቢገልፁልን?**

**አቶ ጳውሎስ፡-** ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ጉዳዮች መካከል በአገር ውስጥ ያሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ልምድ ካላቸው ጋር አቀናጅቶ ውጤታማ ማድረግ አንዱ ነው። አብዛኛዎቹ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ካሉባቸው በርካታ ተግዳሮቶች መካከል የፋይናንስ አቅርቦት ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳል። በዚህ ረገድ ያለው ችግር እጥረት መኖር ብቻ ሳይሆን ለብድር ዋስትና ማስያዣነት አምራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት መስፈርትም ካለው ነባራዊ ሁኔታና ከአምራቾች አቅም አንጻር ሲመዘን ተገቢ አይደለም። በአንድ ወገን ብድር ለመበደር ከሚፈልጉት መጠን ከሁለት እስከ ሰባት በመቶ ተቀማጭ እንዲኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህንን በአይነት ለማስያዝ የሚፈልጉ ከሆነ ደግሞ ቤትና መኪና ብቻ በዋስትና ማስያዝ ይፈቀድላቸዋል።

ይህ ገና በዓመታት እቅድ ውስጥ ጥሪት ቋጥሮ ራሱን ችሎ ሀብት ወደ ማፍራት ብሎም መኪናና ቤት ለመግዛት ለሚውተረተር አምራች እንኳን የሚሞከርም የሚታሰብም አይደለም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፎ ለመበደር እድሉን የሚያገኝ አምራች ቢኖር እንኳን ወለዱ አስራ ስምንት በመቶ የሚደርስ በመሆኑ ሰርተው ለመለወጥ ላሰቡ ጀማሪዎች የሚሞከር አይሆንም። በሌላ በኩል ኢንዱስትሪው እንደ አጠቃላይ ካለበት ችግር ስልሳ በመቶውን ድርሻ የሚይዘው የግብአት እጥረት ነው። ዛሬም ቢሆን በአብዛኛዎቹ አምራቾች የሚጠቀሟቸው ግብአቶች በዶላር እንደ ህንድና ቻይና ከመሳሰሉ አገራት ተገዝተው የሚመጡ ጥሬ እቃዎችና

# ተጠየቅ

መለዋወጫዎችን ነው። የውጪ ምንዛሬ እጥረት ደግሞ ለአምራች ኢንተርፕራይዝ ብቻ ሳይሆን እንደ አገር ያለ ፈተና ላይ ያለንበት ወቅት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም የውጪ ምንዛሬ ከባንኮች እየጠበቁ ከመኖር ይልቅ የውጪ ምንዛሬ ሊያስገኝ የሚያስችል መንገድ ካለ ማማተርና ያለውንም የውጪ ምንዛሬ በአግባቡ ቅድሚያ ለሚሰጠው ጉዳይ ብቻ በቁጠባ መጠቀም ያስፈልጋል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በማምረት አቅም አጠቃቀም ረገድም ሰፊ ክፍተት አለ፤ በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ ኢንተርፕራይዞች እየሰሩ ያሉት ከማምረት አቅማቸው ሀምሳ በመቶ ብቻ ነው። በገበያው ውስጥ እንዲቆዩ የሚረዳቸው በዋናነት ገበያው ውድድር የሌለበት በመሆኑና እጥረት መኖሩ ሲሆን፣ በአቅማቸው ባለማምረታቸው የሚጨምረውን የማምረቻ ዋጋ የሚያካክሱት በተገልጋዩ ላይ ዋጋ በመጨመር ይሆናል።

በሌላ በኩል በአገሪቱ በአሁኑ ወቅት ከአስራ ሁለት በላይ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተው ወደ ስራ ገብተዋል። በእነዚህ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እየገቡ ያሉት በዓለም አቀፍ ደረጃ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ኢንዱስትሪዎች ናቸው። አንዳንዶቹ በተለያዩ አገራት በመቶዎች የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች ያሏቸው ናቸው። በመሆኑም ለእነዚህ ኢንዱስትሪዎች የግብአት እጥረት የሌለባቸው ገበያ የማግኘት ጉዳይ የሚቸግራቸው ባለመሆኑ በቂ የገበያ ትስስር የቴክኖሎጂ አጠቀቃምና ጠንካራ የፋይናንስ አቅም ያላቸው ናቸው።

ነገር ግን እነዚህ ኩባንያዎች አንዳንድ ጊዜ እነሱ በዋናነት ከሚያመርቱት ምርት በተጨማሪ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በቀላል ማሽኖች ሊመረቱ የሚችሉ ስራዎችም ይኖራቸዋል። እነዚህን ፋብሪካዎቻቸውን ባቋቋሙባቸው አገራት ለሚገኙ አምራቾች በማስተላለፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በሌሎች አስመርተው ለገበያ ያቀርባሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የግብአት አቅርቦትንም ሆነ የተመረተውን ምርት በወቅቱ የሚቀበሉት እነሱ በመሆኑ ከላይ የተነሱት የግብአትና የገበያ ችግሮች ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች መሰናከል አይሆንም። የገበያ ትሰስር ብቻ ሳይሆን ፈጣንና ውጤታማ የቴክኖሎጂ ሽግግር የውጪ ገበያ ልምድ እንዲኖር የሚረዳ ይሆናል። በአንጻሩ ትልልቆቹም ኩባንያዎች የሚፈልጓቸውን ምርቶች በከፍተኛ ወጪ ከሌሎች አገራት ከማስገባት በመዳን በቀላሉ በአገር ውስጥ የሚያገኙበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ እድል እስካሁን በኢትዮጵያ በሚጠበቀው ደረጃ ጥቅም ላይ ሳይውል የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በልማቱ በኩል ለመተግበር እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

የሌሎች አገራት ተሞክሮዎች እንደሚያመለክቱት፤ በቅድሚያ ትልልቆቹ ኢንዱስትሪዎች አመኔታ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ለዚህም ኩባንያዎቹ ስምምነት ከማድረጋቸው በፊት ፋብሪካው ያለበት ሁኔታ፣ የሰራተኛ አያያዝ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የተረፈ ምርት አወጋገድና ተያያዥ ጉዳዮችን ማጣራት ይፈልጋሉ። የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትም በአገሪቱ ያሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም በማጎልበት ትስስር እንዲኖር ለማስቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እየሰራ ይገኛል። ይህ አካሄድ በተለይ በመካከለኛው ምስራቅ በማደግ ላይ ባሉ አገራት ከዓመታት በፊት ተሞክሮ ውጤት ያስመዘገበ ነው። በአሁኑ ወቅትም ከልማት ባንክ ጋር በመሆን የህግ ማእቀፍ ከማሰናዳትና የተለያዩ ማበረታቻዎችን ከማድረግ ጀምሮ ዘርፉን በትስስር ውጤታማ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል።

በተጨማሪም በኢንተርፕራይዞች መካከል ያለው ትስስር መዳበር የጎንዮሽ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችልም ይሆናል። በዚህም በሂደት አነስተኛ ከአነስተኛ፣ አነስተኛ ከመካከለኛ፣ መካከለኛ ከከፍተኛ፣ ከፍተኛ ከከፍተኛ፣ የማስተሳሰር ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል። ይህ የሚጠቅመው የአንዱ ምርት ለሌላው ግብአት ስለሚሆን እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችም በቀጥታ የውጪ ገበያውን ለመቀላቀል ከመሞከር ይልቅ ልምድ ካካበቱት ጋር በቅንጅት በመስራት አቅማቸውን ካዳበሩ በኋላ ቢሞክሩት የተሻለ ውጤታማና

**ጥቃቅንና አነስተኛ ላይ የሚሰሩት በእድገታቸው ልክ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ሲያድጉ ግብር ከፋይ ይሆናሉ። ስለዚህ ማደግን አይፈልጉም። በማደጋቸው ቀደም ሲል የሚያገኙትን ስስኬታቸው አጋዥ የሆነውን ጥቅም ማጣት አይፈልጉም። ከግብር ከፋይነት በላይም ሲያድጉ የመስሪያ ሼዱን ስለሚለቁ ከማደግ ይልቅ አለማደጋቸውን ምርጫ አድርገዋል**

ዘላቂ ስለሚያደርጋቸው ነው። ይህ ሂደት ለአገር ውስጥ አምራቾች ከብዛት ለረጅም ጊዜ ማትረፍ የሚያስችላቸው ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ በጠቀሷቸው ጉዳዮች ላይ የልማት ባንክ እያከናወነ ያለው ተግባር ምንድን ነው?**

**አቶ ጳውሎስ፡-** ልማት ባንክ እንደሚታወቀው የፖሊሲ ባንክ ነው። የፖሊሲ ባንክ ማለት የመንግስትን ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ስራዎችን የሚሰራ ባንክ ነወ። ከዚህ አንፃር በልማት ባንክ በኩል ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት የፋይናንስ ፕሮጀክት ይዞ እየሰራ ነው። መጀመሪያ ላይ ወደ 76 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በዓለም ባንክ ብድር መጥቶ ለተቋማቱ የስራ ማስኬጃና የማሽነሪ ብድር አቅርቦት እንዲያገኙ ይሰራል።

ልማት ባንክ በዚህ መልኩ እነዚህን ተቋማት በመደገፍ የስራ እድል እንዲፈጠር ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲያበድሩ የሚያደርግባቸው ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችም አሉ። እነዚህን አበዳሪ ተቋማት በአገሪቱ አጠቃላይ ባሉት ቅርንጫፎች ብድር እየሰጡ ይገኛል።

ማሽነሪ አቅርቦትም ቢሆን አራት ማሽን አቅራቢ የሆኑ ልማት ባንክን ጨምሮ አምስት ተቋማቱ 20 በመቶ ቁጠባ ካካሄዱ በኋላ ሌላ መያዣ ሳይጠየቁ ማሽኑ ራሱ መያዣ ሆኖ ይቀርባል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ልማት ባንክ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የመስሪያ ማሽንንና ስራ ማስኬጃ ገንዘብ በማቅረብ ስራቸውን እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ችግሮች አሉ፤ ከእነዚህም መካከል አንደኛ ኢንተርፕራይዞቹ ገንዘብ የሚያገኙበት መንገድ የአበዳሪ አበዳሪ መሆኑ በራሱ ችግር አለው። ይህ ሲባል ልማት ባንክ ለማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ያበድራል፤ እነሱ ደግሞ ለተቋማቱ ያበድራሉ። በዚህ ሂደት የመበደሪያ የወለድ ምጣኔው እስከ 18 በመቶ እንዲሄድ ሆኗል። ስለዚህ የመንግስት ፖሊሲውን የማስፈፀሙ ነገር አጠያያቂ ይሆናል።

አሁን ያለው የኢኮኖሚ ስርአት ገበያ መር ቢሆንም ገና ስራ ጀምረው ወደ ምርት ያልገቡ አነስተኛ አምራቾች ግን ድጋፍ ካልተደረገላቸው ተወዳዳሪነታቸው ቀርቶ ከገበያ ሊወጡ ይችላሉ። ለስራ እድል ፈጠራ ጠቀሜታ ያላቸው እነዚህ ተቋማት ድጋፍ ካልተደረገላቸው የታሰበው የስራ አጥ ቁጥር የመቀነስ ነገር አይሳካም እንደማለት ነው።

የልማት ባንክ ሲበደር በውጭ ምንዛሪ ይበደራል፤ ለማይክሮ ፋይናንስ ተቋማቱ ግን በብር ነው የሚሰጠው። ከውጭ ግብኣት ማምጣት የፈለገ አምራች የውጭ ምንዛሪን ስለማያገኝ ይህም ለስራው ተግዳሮት ይሆናል።

ኢንተርፕራይዞቹ ብድር ተበድረው አይመልሱም ይባላሉ፤ ግብአት ካላገኙ እንዴት አድርገው ሊመልሱ ይችላሉ? ብድር ዛሬ ጠይቀው የዛሬ 6 ወር የሚደርስ ከሆነ የዋጋ ግሽበቱ ጋር ካልተመጣጠነ ምን ዋጋ አለው? ዛሬ የአንድ ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት የዛሬ ስድስት ወር አራት ሚለዮን ብር ሊሆን ይችላል። ብድር የሚጠይቅበት ጊዜና ገንዘቡ እጅ የሚገባበት ጊዜ ረጅም መሆኑ የራሱ ተግዳሮት አለው። በአጠቃላይ ዘርፉ በአስፈላጊ ግብአቶች ረገድ ፈጣን ምላሽ ባለማግኘታቸው ምክንያት እየተበረታታ አይደለም። ይህ ችግር መኖሩንም እንደ ተቋም ለልማት ባንክ አቅርበናል፤ ፖሊሲው መሻሻያ ከተደረገ በኋላ ለውጥ ሊኖረው ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- በብድር መያዣ ረገድ ተቋሙ የሄደበት ርቀት እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ጳውሎስ፡-** በብሄራዊ ባንክ በኩል ለብድር መያዣነት ሌሎች ነገሮችም ያስያዙ እንዲሆኑ እየተሞከረ ነው። ለምሳሌ ለአርሶ አደር ከሆነ እንስሳቱን ማስያዝ እየተፈቀደ ነው። ስለዚህ ከቤትና ከመኪና ውጪ የሆኑትን ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ሀብቶችን ለማስያዝ እየተሞከረ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአገር ውስጥ አምራቾች እንኳን ወደውጭ አገር ስሚልኩት ምርት ይቀርና ለአገር ውስጥ የሚያቀርቡት ምርት ላይ የጥራት ጉዳይ አጠያያቂ እየሆነ ነው፤ እዚህ ላይስ ምን አይነት ስራዎች እየተሰሩ ነው?**

**አቶ ጳውሎስ፡-** በአደጉት አገራት የጥራት ጉዳይ ለድርድር ስለማይቀርብ ከጥራት ደረጃ በታች ምርቶች አይመረቱም። በእኛ አገር ግን ምንም አይነት እቃ ቢመረት ገቢ የማያጣበት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ የማህበረሰቡ ግንዛቤ ማነስ፤ አንዳንዴም አማራጭ ማጣትም ስለሆነ ያለ ምንም ጥያቄ ገበያ እንዲያገኝ ሆኗል።

ማህበረሰቡ ጥራት የሌላቸውን ምርቶች ባይጠቀሙ ግን አምራቾች የጠራ ስራ መስራት ይችላሉ። ማህበረሰቡ በቂ ግንዛቤ ካለው በጥራት የማይደራደር ማህበረሰብ መፈጠር ከቻለ ጥራት ይመጣል ብዬ አስባለሁ። ወደ ውጭ ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶችም በጥራት የተሻሉ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ሁሉም አምራቾች ለውጭ ገበያ እንዲያመርቱ ከማድረግ ይልቅ የተወሰኑት ለአገር ውስጥ፤ ሌሎቹ ደግሞ ተነጥለው ለውጭ ገበያ አቅርቡ ቢባልና በዚህ ልክ ድጋፉም ጥራቱም ላይ ቢሰራ የተሻለ አማራጭ አይሆንም?**

**አቶ ጳውሉስ፡-** በእርግጥ ሁሉም ምርት ወደውጭ እንዲሄድ አይደረግም። ለምሳሌ የመከላከያ ልብስ፣ የእንጨትና የብረታ ብረት ስራዎችና ሌሎችም ወደውጭ እንዲሄድ አይደረጉም። አሁን ለውጭ ገበያው የሚቀርበው በመሰረታዊነት የግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ነው። ኤክስፖርት ማድረግ በራሱ ግን ለጥራት የሚሆኑ ምርቶች ገበያው ውስጥ እንዲበዙ፤ የአገራችንም ኢንዱስትሪዎች እያደጉ እንዲሄዱ ያደርጋል።

**አዲስ ዘመን፡- በበጀት ዓመቱ ተቋሙ የሰራቸው ስራዎች ምን ምንድን ናቸው?**

**አቶ ጳወሉስ፡-** የተቋሙ ግብ የተቀመጠው አንደኛ የስራ እድል በመፍጠር ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ተኪ ምርቶችን ማምረት ነው። በበጀት ዓመቱ የስራ እድል ከሰባ በመቶ በላይ ተሳክቷል።ውደ ውጭ አገር የሚላኩ ምርቶችን ማምረት 72 በመቶ፤ ተኪ ምርት ግን ገና ምንም ያልተሰራበት ነው።

እንደ አገርም መተካት የሚለው ሀሳብም በደንብ ግንዛቤ ያልተያዘበት ነው።ሁሉም ምርት ይተካል አይተካም የሚለው እንዲሁም የትኛውን ለመተካት ታቅዷል የሚለውን እያስጠናን ነው። በአጠቃላይ ግን የበጀት ዓመቱ አፈፃፀም አርኪ የሚባል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- "ኢትዮጵያ ታምርት" በሚል መርህ በአገር አቀፍ ደረጃ የተያዘ ትልቅ ንቅናቄ መኖሩ ይታወቃል፤ በዚህም በርካታ ተኪ ምርቶች እንደሚመረቱ ተነግሯል፤ በዚህ ረገድ ምን አይነት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው?**

**አቶ ጳወሉስ፡-** አዎ! ኢትዮጵያ ታምርት የሚል ንቅናቄ ተፈጥሯል። እሱ ግን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኃላፊነት ስለሆነ መልሱን እነሱ እንዲመልሱ ብናደርግ መልካም ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት ዓመታት በኮቪድ 19 ወረርሽኝ እና በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው ጦርነት የአገሪቱ ኢኮኖሚ መፈተኑ የሚታወቅ ነው፤ ዘርፉ በዚያ አስከፊ ወቅት ችግሮቹን የተቋቋመው እንዴት ነበር?**

**አቶ ጳወሉስ፡-** ኮቪድ 19 በዓለም ላይ ከፍተኛ የሆነ ቀውስ አስከትሎ ነበር። በተለይ አምራች ኢንዱስትሪውን የጎዳበት ሁኔታ አለ። ወደ እኛ አገር ስንመጣ አምራች ኢንዱስትሪው ተጨማሪ እድል ያገኘበት ሁኔታ ነበር። ለምሳሌ በአነስተኛ ደረጃ ጋርመንት ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩት ማስክ በማምረት ወደ ውጭ እስከመላክ የደረሱበት ሁኔታ ነበር።

ሳኒታይዘር ማምረት እንዲሁም የጽዳት መጠበቂያ እቃዎችና በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ስለነበር አነስተኛ አምራቾች ላይ ይህ ነው የሚባል ጉዳት አልደረሰባቸውም። በጦርነቱም ሆነ በኮረና ግን ጉዳት የደረሰባቸው ድጋሚ እንዲያገግሙ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። በዚህም ውጤት እየታየ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ስቃስ ምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ጳወሉስ ፤** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው።የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል።ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል።በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ባይተዋርነት ያሳሸነፋቸው ምሁራን

## የመነሻ ሀሳብ

የመነሻ ሃሳቡን የተዋስኩት እንደ “መዝሙረ ዳዊት” ደጋግሜ ከዘለቅሁት የአንድ መጽሐፍ ይዘት ነው።የመጽሐፉ ርዕስ “ፋና ወጊ የለውጥ አቀንቃኞች በኢትዮጵያ፤ በሃያኛው መቶ ዓመት መባቻ” የሚል ሲሆን ደራሲው እውቁ የሀገራችን ምሁር ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ናቸው።የመጽሐፉ የእንግሊዘኛ ቅጂ “Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist of the Early Twentieth Century” በሚል ርዕስ ከአንባቢያን ዘንድ የደረሰው እ.ኤ.አ በ2002 ዓ.ም ሲሆን የአማርኛ ትርጉም ደግሞ ከአሥር ዓመት በኋላ በ2013 ዓ.ም ታትሞ በመነበብ ላይ ነው።

ጎምቱው የመጽሐፉ ደራሲ ሀገሪቱ ካፈራቻቸው የታሪክ ዘርፍ ምሁራን አንዱና በታሪክ ስነዳና በማስተማር ሙያቸው በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ጥቂቶች መካከል አንዱ ናቸው።እስከ ዛሬ ላበረከቱት ዘርፈ ብዙ ሀገራዊ አገልግሎታቸው ያለማመስገን ንፉግነት ስለሆነ “ክብረት ይስጥልን፣ ጤናን ከዕድሜ በረከት ጋር ያጎናጽፍልን” ብሎ መመረቁ አግባብ ይሆናል።

ደራሲው ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ምክንያት የሆናቸውን አጋጣሚ በመቅድሙ ክፍል እንደሚከተለው ማስታወሻ አኑረዋል።“[በዚህ መጽሐፍ ውስጥ] ታሪካቸው የቀረበው ምሁራን መጀመሪያ ትኩረቴን የሳቡት በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ነው።አስተማሪዬ ሪቻርድ ኮክ በ1918 እስከ 1928 ድረስ ይታተም በነበረው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ይወጡ የነበሩትን መጣጥፎች ዝርዝር ማውጫ እንዳዘጋጅለት ሥራ በሰጠኝ ወቅት ነበር” በማለት የመጀመሪያ ገጠመኞቻቸውን ካስታወሱ በኋላ ይበልጥ ስሜታቸው የተነሳሳው ደግሞ በተማሩበት በዚያው ዩኒቨርሲቲ ከመጽሐፉ ጋር ተመሳሳይ ርዕስ ያለው የታሪክ ትምህርት ኮርስ በተከታታይ ሲያስተምሩ እንደነበርም ገልጸዋል።

ይህ ጸሐፊም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ስሜቱ የተጋባበት በመጽሐፉ ውስጥ የታጨቀው የዘመኑ ምሁራን ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶች እጅግ የሚማርኩና ዛሬያችንን በራሳችን ዐውድ እንድንፈትሽ ጭምር ግድ የማለት አቅም እንዳለው ስለተረዳሁ ጭምር ነው።

ደራሲው መጽሐፉ በሸፈነው የሃያ አንደኛው መቶ ዓመት መባቻ የነበሩትን ምሁራን ያስተዋወቁን በሚከተለው ሥዕላዊ ገለጻ ነው፡- “ምሁራኑ ሐሳባቸውን ሲበዛ በሚማርክ ቋንቋና በሚያሳምን አመክንዮ የማቅረብ ልዩ ችሎታ ነበራቸው።ለዐሥራ አንድ ዓመታት በተከታታይ ይወጣ በነበረው ሳምንታዊ የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዓምዶች ላይ በተለያዩ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የጠራ አስተያየት ይሰጡ፤ የደራ ውይይት ያካሂዱ ነበር።ከዚያ አልፎ ብዙዎች ሐሳቦቻቸውን በሚጽፏቸው መጻሕፍት አማካይነት ለመግለጽ በቅተዋል።ከእነርሱ መካከል አንዱ ከሃያ በላይ የተለያዩ መጠን ያላቸው መጻሕፍት ሲደርሱ፤ ሁለቱ ደግሞ የሕይወት ታሪካቸውን አጋርተውናል።”

ለመሆኑ በደራሲው የተዋበ ገለጻ ታሪካቸውና ያበረከቱት ሥራቸው የተተረከላቸውና እንድንተዋወቃቸው የተመረጡት ምሁራን እነማን ነበሩ? ቁጥራቸውና ትሩፋቶቻቸው በ340 ገጾች በዝርዝር የቀረበላቸውን እነዚያን ምሁራን በሙሉ ለማስታወስ ለጋዜጣው የተመደበው ይህ ኩርማን አምድ በቂ ስለማይሆን በወፍ በረር ቅኝት ለማስታወስ የሚሞከረው እጅግ ጥቂቶቹን ብቻ ይሆናል።

ከመቅድሙ ክፍል ቀጥሎ የመጽሐፉን ገጾች መግለጥ ስንጀምር የምናገኘው “ፋና ወጊ” ተብለው የተገለጹትን ምሁራን ፎቶግራፍና ስማቸውን ነው።“ከሺህ ቃላት አንድ ሥዕል የበለጠ ይናገራል” እንዲሉ ወደ ታሪካቸውና “ገድላቸው” ትረካ ከመሸጋገራችን አስቀድሞ ከምስላቸው ጋር እንድንተዋወቅ መደረጉ ታሪካቸውንና አስተዋጽዋቸውን ከፎቶግራፋቸው ጋር ለማገናዘብ ስለሚረዳን ደራሲው አዲስ የአቀራረብ ስልት አስተዋውቀውናልና ለደራሲው ተገቢውን ክሬዲት መስጠቱ አግባብ ይሆናል።

በሥነ ጽሑፍ ኃያሲያን ተደጋግሞ እንደሚገለጸው “ከሺህ ቃላት አንድ ሥዕል የበለጠ መናገሩ እውነትነት ቢኖረውም፤ ከሺህ ቃላት አንድ ሥዕል የበለጠ መናገሩን በአግባቡ ለመግለጽ ሺህ ቃላት እንደሚያስፈልግ ሊዘነጋ አይገባም።” እንዲሉ፤ የምስልና የቃላት ጥምረቱ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

“ፋና ወጊ” ምሁራኑ የተገለጹት በሁለት ትውልድ ተመድበው ነው።የመጀመሪያዎቹ የትውልዱ አባላት “ሁሉም ማለት ይቻላል የምኒልክ ወይንም የድኅረ ምኒልክ ዘመን ተዋንያን ሲሆኑ ትምህርታቸውን የቀሰሙት ደግሞ በሀገር ቤት ወይንም በውጭ ሀገራት ነበር።በሁለተኛው የትውልድ ጎራ የተመደቡት ደግሞ አብዛኞቹ በዘመነ ተፈሪ መኮንን (በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ) ዘመን ነበር።እነዚህ የሁለተኛው ትውልድ ምሁራን በሚያሳዝን ሁኔታ በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራና አገዛዝ ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ” የሀገሪቱ ብርቅዬ ልጆች ነበሩ።

ምሁራኑ የትምህርት ዕድል ያገኙባቸውን አጋጣሚዎችና ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ያበረከቷቸውን ትሩፋቶች የጥቁምታ ያህል የምናስታውሰው የራሳችንን ዘመን ምሁራን ወደ ሃሳባችን እያመጣን መሳ ለመሳ በመፈተሽም ጭምር ሊሆን ይገባል።

ደራሲው የመጀመሪያዎቹን የትውልዱን አባላት ያቧደኑት በአራት ከፍለው ሲሆን የመጀመሪያዎቹን “የዕድል ማደጎዎች” የሚል መለያ ሰጥተዋቸዋል።ምክንያቱ ደግሞ አብዛኞቹ የውጭ የትምህርት ዕድል ለማግኘት የቻሉት “ተዓምራዊ” ሊባል በሚችል ምክንያትና ሰበብ መሆኑን ለማስታወስ ነው።

በቀዳሚነት ከተጠቀሱት “የዕድል ማደጎዎች” መካከል ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ (ዶ/ር ቻርለስ ማርቲን) አንዱ ናቸው።እኚህ ሰው ወደ ውጭ ሄደው ለመማር አጋጣሚው የተፈጠረላቸው አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ወራሪ ጦር እጄን አልሰጥም ብለው ራሳቸውን በራሳቸው እጅ ባጠፉበት አጋጣሚ ትንሹ ወርቅነህ ከንጉሡ ልጅ ከልዑል ዓለማየሁ ጋር በንጉሡ ሬሣ አጠገብ ቆመው ሲያለቅሱ የወራሪው አባል በሆነው በኮ/ል ቻምበርሊን ተወስደው በኋላም ቻርለስ ማርቲን (የፈረንጅኛውን ስም ያገኙት ከእኚሁ ሰው ስም ነው) ለተባሉ ሌላ መኮንን ተላልፈው ከተሰጡ በኋላ ነበር።

ሐኪም ወርቅነህ በህንድና በተለያዩ ሀገራት ከፍተኛ የሕክምና ትምህርታቸውን ተከታትለውና ሙያቸው ዳብሮ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በአፄ ምኒልክ ዘመን በተለያዩ ኃላፊነቶች ሀገራቸውን አገልግለዋል።ለአብነት ያህልም፡- የንጉሡ ነገሥቱ ሐኪም፣ በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር፣ የፍልውሃ አስተዳዳሪ፣ የተፈሪ መኮንን ት/ቤት አስተዳዳሪ፣ ደራሲ፣ የበጎ አድራጎት ማኅበር መሥራች፣ ጣና ሐይቅ ላይ ሊሠራ ለታቀደው ግድብ በአሜሪካ በተደረገው ውይይት የተደራዳሪ ቡድን አባል፣ ከውጭ ሀገራት ጋር ሙግት ሲያጋጥም ፍትሕ እንዲሰጥ ለተሰየመው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶች አስፈጻሚ ወዘተ. በመሆን የድርሻቸውን የሀገር ጥሪ አደራ ተወጥተዋል።“የሰለጠንኩበት ሙያ ስላይደለ በዚህ ቦታ አትመድቡኝ” ብለው አለመከራከራቸውን ልብ ይላል።ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ባለመስማማትም እስከ መጋጨት የደረሱ ቢሆንም የዜግነታቸውን ግዴታ ከመወጣት ግን አልቦዘኑም ነበር።

ከአፄ ምኒልክ ዘመን ቀጥሎም “ከዝነኛዋ የኢትዮጵያ መብት ተሟጋች ከሲልቪያ ፓንክረስት ጋር በመቀናጀት እርሷ ባቋቋመችው ‹New Times and Ethiopia News› በተሰኘው ጋዜጣ አማካይነት የእንግሊዝን አቋም በመሞገትና በማጋለጥ ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል” (ገጽ 62)።ሁለቱ ልጆቻቸው ዮሴፍና ቢንያም ወርቅነህ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በግራዚያኒ ላይ የተሞከረው ግድያ ሰበብ ሆኖ ከሌሎች የተማሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር ታፍሰው ተገድለዋል።በርካታ ቤተሰቦቻቸውም ወደ ኢጣሊያ ተግዘዋል።

ሌላውና በዘመኑ “ፋና ወጊነት” የሚጠቀሱት ምሁር ከንቲባ ገብሩ ደስታ ናቸው።የመጽሐፉ ደራሲ ከንቲባ ገብሩን የገለጹት “የእርሳቸው ሕይወት ትውልድ ተሻጋሪ ነበር” በማለት ነው።ገብሩም ልክ እንደ ወርቅነህ ሁሉ ወደ ውጭ የመውጣትና የመማር ዕድል የገጠማቸው የወራሪው የእንግሊዝ ጦር ምርኮኛ በመሆን ነበር።የውጭውን ኑሮ ተላምደውና ተምረው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላም ከከንቲባነት እስከ ዲፕሎማትነት ያገለገሉ ተጠቃሽ ባለውለታ ናቸው።

አኔሲሞስ ነሲብ በባሪያ ፈንጋዮች ተጠልፈው ከሀገር ቢወጡም የኋላ ኋላ በትምህርታቸው ከፍታ ላይ ደርሰው ወደ ሀገራቸው በመመለስ መጽሐፍ ቅዱስን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በመተርጎም ላቅ ያለ ውለታ የዋሉ የታላቅ ሰብእና ባለቤት ነበሩ።

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ በምፅዋ ወደብ መልሕቋን ጥላ የቆመችን መርከብ ለመጎብኘት ብለው ከገቡ በኋላ ተሸሽገው ከሀገር በመውጣት ዕድል ገጥሟቸው በበርሊን ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ተከታትለው ወደ ሀገራቸው በመመለስ የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ረዳት ሐኪም፣ በአዲስ አበባ ጅቡቲ ምድር ባቡር ኢንስፔክተርና በኋላም የድሬዳዋ ነጋድራስ በመሆን ካገለገሉ በኋላ በ33 ዓመታቸው በአጭር የተቀጩ ምሁር ነበሩ።እኚህ ተመስጋኝ ምሁር “አፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ” እና “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” በሚሉ ርዕሶች ያዘጋጇቸው ሁለት መጻሕፍታቸው ዛሬም ድረስ ለተመራማሪዎች ዋነኛ የዘመኑ ማመላከቻ ሆነው እየተጠቀሱ ይገኛሉ።

ከብዙዎች መካከል የተመረጡት ተጠቃሽ ፋና ወጊዎች የሚያመሳስላቸው አራቱም ወደ ውጭ ሀገር የሄዱት ዕድልና አጋጣሚ ባመቻቹላቸው እጅግ በሚገራርሙ አጋጣሚዎች መሆኑ፤ በየሄዱባቸው ሀገራትም ከልበ ቅኖች ባዕዳን ዜጎች ሞገስ አትርፈው እስከ ከፍተኛ ደረጃ የመማር ዕድሎች ማግኘታቸው፤ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላም ዘመኑና መሪዎች በፈቀዱላቸው መስክ እንጂ በሰለጠኑበት ሙያ የሙጥኝ ብለው “ምን ሲደረግ” በማለት ፎክረው ወይንም አኩርፈው በዳግም ስደት ሀገራቸውን ጥለው ሲሸሹ አናነብም።ከሰለጠኑባቸው የዕውቀት ዘርፎች ይልቅ ቅድሚያ የሰጡት “ለእናት ሀገራቸው ፍቅር” መሆኑ ሁሉንም ያመሳስላቸዋል።

ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ገድለኞች ታላላቅ የሕይወት ታሪክና የመስዋእትነት ፍጻሜ ለመዘርዘር ሞክሮ ከቁጥራቸው ብዛት የተነሳ ማንን ጠቅሶ ማንን እንደሚተው ቢጨንቀው ልክ እንደዚህ አምደኛ የተወሰኑትን ብቻ ከዘረዘረ በኋላ ሃሳቡን ለማጠቃለል የሞከረው፤ “እንግዲህ ምን እላለሁ…ስለ ጌዲዎን፣ ስለ ባርቅ፣ ስለ ሶምሶን፣ ስለ ሳሙኤል፣ ስለ ነብያት እንዳልተርክ ጊዜ ያጥረኛል።” ካለ በኋላ “እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን አሉልን” በማለት ሃሳቡን ይደመድማል።

ይህ ጸሐፊም ስለ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ስለ አለቃ ታዬ ገብረ ማርያም፣ ስለ አፅመ ጊዮርጊስ ገብሩ፣ ስለ ብላታ ገብረ እግዚአብሔር ጊላ ማርያም፣ ስለ ብላታ ዴሬሳ አመንቴ፣ ስለ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ስለ ከንቲባ ነሲቡ ዘማኑኤል፣ ስለ ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ፣ ስለ ልዑል ራስ መኮንን እንዳልካቸው፣ ስለ ፕሮፌሰር ታምራት አማኑኤል ወዘተ. ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ ተምረው ወደ ሀገራቸው በመመለስ በሙያቸው ያለመቆጠብ ማገልገላቸውን በዝርዝር ቢተርክ በወደደ ነበር።ሁሉም ዘመኑ በፈቀደላቸው ልክ አሻራቸውን አሳርፈው አልፈዋል።እርግጥ ነው አንድ ሁለቱ ለወራሪዎቹ ጣሊያኖች ይወግኑ ነበር እየተባሉ ተተችተዋል፤ በጥፋታቸው ልክም ተገስጸዋል።ድካማቸውና ጥፋታቸው ግን ደማቅ የፋና ወጊነታቸውን ብርሃን ሊያደበዝዝ አልቻለም።

እነዚህ የዘመናቸው ከዋክብት ሀገራቸውን ያገለገሉት በተመቻቸ የሥልጣን ወንበር ላይ ተቀምጠው አልነበረም።“ሰማይ አይታረስ፤ ንጉሥ አይከሰስ” የሚለው የዘመኑ ብሂል፣ ወግና ባህሉ ገደብ ሳይጥልባቸው በነፍሳቸው እየተወራረዱም ቢሆን የየዘመናቸውን መሪዎች የአስተዳደር ፖሊሲ በድፍረት ተችተዋል፣ አማራጭ ሃሳቦችንም በነፃነት አቅርበዋል።ከመደበኛ ሙያቸው እልፍ በማለትም የሀገራቸውን የዲፕሎማሲ ክፍተት ለመሙላት ሞክረዋል።

በየስብሰባውና በየምክክር መድረኩ እየተገናኙ የሃሳብ ፍጭት አድርገዋል።በጋዜጦች አምድ ላይ ሃሳባቸውን እያንሸራሸሩ ተከራክረዋል።ሀገራቸው በጠላት በተወረረችበት ወቅትም ነፍጥ አንግበው ተፋልመዋል።በሴራ ፖለቲካ ተጠልፈውም ተንገዳግደዋል።ሹመትን ብቻ ሳይሆን ሽረትንም በፀጋ ተቀብለው “ነገም ሌላ ቀን ነው” በማለት ክፉ ቀናትን በትእግሥት አሳልፈዋል።በዚህ ሁሉ መካከል ግን ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ታማኞች ነበሩ።ሀገራቸው ዘምና ለማየትም ጉጉዎች ነበሩ።በአንድ ዐረፍተ ነገር እንጠቅልለው ካልን የሕይወታቸው መርህ የነበረው “ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን፤ እኔ ለሀገሬ ምን አደረግሁላት” የሚል ነበር።

### «እኔስ?» የጠቢብ ሰው መልስ፤

ዛሬም ሀገሬ የምሁራን ደሃ አይደለችም።እውነት እውነቱን እንመስክር ካልን በኢትዮጵያ “የረከሰ ሀብት” ምንድን ነው ተብሎ ቢጠየቅ “ምሁራንና የምሁራን እውቀት” የሚለውን መልስ የሚሰጡ ብዙዎች ናቸው።ኢትዮጵያ ምህዳሯን በስፋት የዘረጋችው ለባለ እውቀቶች ሳይሆን ለግል ጥቅም ለሚተጉ ተዋንያንና ተዋንያት ስለመሆኑ በድፍረት ባንመሰክር ትዝብት ላይ እንወድቃለን።

“እኔ ለሀገሬ!” የሚለው መርህ ሟሙቶና ቀጥኖ “እኔ ለጎጤ ብቻ፣ እኔ ለብሔሬ ብቻ፣ እኔ ለግሌ ባህልና ወግ ብቻ፣ እኔ ለቅርቤና ለብጤዬ ብቻ፣ እኔ ለፖለቲካ አቋሜ ብቻ ወዘተ.” ወደሚል ወደ ነፍስና የራስ ጥሪ ፍልስፍና ከዞረ ዓመታት ተቆጥረዋል።ምናልባትም የትውልዳችን ዋና መገለጫም ሳይሆን የሚቀር አይመስልም።ከሥልጣና በፊት ሥልጣን ስለሚቀድምም መንገዶች ሁሉ አንድም ተጠላልፈዋል፤ አንድም ተቆላልፈዋል።

ብዙውን ጊዜ የሚደመጠውና የሚስተዋለው ኢትዮጵያን ማዕከል ያደረገ የሃሳብ ፍጭት ሳይሆን የጎጥ ቁጭትና ብሽሽቅ ወደ መሆን ሥር ሰዷል።ተምሮ በመመለስ ሀገርን ከማገልገል ይልቅ እንደ ወጡ መቅረት በእድለኛነት የሚያስፈርጅበት ወቅት ላይ ደርሰን ይሆንን አሰኝቶ ያስተክዛል።አብዛኞቹ የሀገሬ ምሁራን “ከራስ በላይ ነፋስ” ያንገዳገዳቸው ይመስላል።ወይንም “በዝም አይነቅዝም” ቁዘማ ውስጥ ተመስጠዋል።ጥቂት የማይባሉ ዘመንኞቹ ምሁራንም በራቸውን ከውስጥ ቆልፈው የውጭውን ትርዒት የሚመለከቱት በማጮለቅ ዓይነት ስጋትና ፍርሃት ይመስላል።በርከት የሚሉት ብዙኃንም ዓላማው ፍንትው ብሎ በማይታይ የፖለቲካ ዳፍንት ከግራ ከቀኝ እየተላጉ ሀገሪቱንም ሲያላጉ እያስተዋልን ነው።

እጅግ ጥቂት የሚባሉት ምሁራን ግን ሙያቸውን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ጭምር ለኢትዮጵያ መልካምነት “አሥራት ሰጥተው” እንደ ጧፍ እየነደዱ፤ ደማቅ ብርሃን በመፈንጠቅ የሀገሪቱ ጨለማ እንዲገፈፍ እየተጉ እንዳሉም በአክብሮት እናስታውሳለን።የዛሬዎቹ የሃያ አንደኛው መቶ ዓመት መባቻ ፋና ወጊ የሀገሬ ምሁራን ፈተና ለሀገር እድገት መታገል ብቻ ሳይሆን ከራሳቸውም ጋር ትግሉን አፋፍመው ከባይተዋርነት ነፃ ቢወጡ ኢትዮጵያችን ደምቃ ለመክበር ጊዜ አይፈጅባትም ነበር።ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## «ዘርፉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን እስከ 40 በመቶ ቅናሽ ለሸማቹ እያቀረበ ነው»

*- አቶ መህዲ አስፋው*
*የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ዋና ሥራ አስፈጻሚ*

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በስሩ ከሚገኙ አራት ዘርፎች መካከል የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ/ኢትፍሩት/ አንዱ ነው።ዘርፉ "ኢትፍሩት" ተብለው በሚታወቁት መሸጫ ኮንቴነሮቹ በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ለሸማቾች በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ይታወቃል።

በዛሬው የንግድና ግብይት አምዳችን ይህ ዘርፍ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ለሸማቾች በማቅረብ እያከናወነ ያለውን ተግባርና የድርጅቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ ከአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መህዲ አስፋው ጋር ያደረግነውን ቆይታ ይዘን ቀርበናል።መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፦ የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ተግባራት ቢያብራሩልኝ?**

**አቶ መህዲ፦** የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን ይዞ ይሰራል። በቀዳሚነት አምራቾችን የመደገፍ አላማ ያለው።ይህም ሲባል አምራቾች አምርተው ገዢ እንዳያጡ ካሉበት ቦታ ሄዶ ይገዛል።በተለይም ዋጋ በሚቀንስበት ጊዜ ከአዲስ አበባ ከተማ ራቅ ባሉ አካባቢዎች ጭምር በመሄድ ምርታቸውን ያነሳል።በዚህም ሸማቾች ምርቱን እንዲያገኙ እድሉን ይፈጥራል።ሁለተኛው ከአምራቹ የመጣውን ምርት ከተማ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም በክልል ከተሞች በሚገኙ ማከፋፈያዎችና የሽያጭ መደብሮች አማካኝነት በተመጣጣኝ ዋጋ ያከፋፍላል።

በተያዘው 2015 በጀት አመት ባለፉት ሰባት ወራትም 40 ሺ ኩንታል የሚደርሱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ከተለያዩ አካባቢዎች ገዝቶ ለተጠቃሚው ማሰራጨትና ማከፋፋል ችሏል።ይህም በገንዘብ ሲተመን 150 ሚሊዮን ብር ይደርሳል።በሰባት ወራት ውስጥ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ካደረጋቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አይነቶች ከፍራፍሬ ምርት በዋናነት ብርቱካን፣ ማንጎ፣ ሙዝ፣ ከአትክልት ምርት ደግሞ ቲማቲም፣ ድንች፣ ስኳር ድንች ይጠቀሳሉ።

**አዲስ ዘመን፦ ለገበያ ራቅ ባሉ አካባቢዎች የሚገኙ አምራቾች ምርት አምርተው ገበያ ሲያጡ ምርቱ የሚበላሽበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ለዚህ ችግር የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ አምራቹን እንዴት እያገዘው ይገኛል?**

**አቶ መህዲ፦** የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፉ ረጅም ርቀት ተጓጉዞ ከአምራቹ ምርቱን በመግዛት አምራቹ ተጠቃሚ እንዲሆንና በቀጣይም የማምረት ፍላጎት እንዲኖረው ያበረታታል።ባለፈው ዓመት ከአዲስ አበባ ዘጠኝ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት በሚገኘው በደቡብ ኦሞ ዳሰነች ወረዳ ውስጥ በመግባት የሰራበትን ሁኔታ በአብነት መጥቀስ ይቻላል።በወቅቱ የክልሉ መንግሥት በአካባቢው የሚገኙ አርብቶ አደሮችን ወደ ከፊል አርሶ አደር ለመለወጥ በያዘው ፕሮጀክት በርካታ አርሶ አደሮች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን አምርተው ነበር።ነገር ግን በአካባቢው መሰረተ ልማት የተሟላ ባለመሆኑ ወደ አካባቢው ገብቶ ምርቱን የሚገዛ ነጋዴ ባለመኖሩ አርሶ አደሮቹ ያመረቱትን ምርት ለገበያ ማቅረብ አልቻሉም ነበር።በመሆኑም የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ወደ አካባቢው በመጓዝ ምርቶቹን ገዝቶ ወደ ማዕከላዊ ገበያ እንዲቀርቡ አድርጓል።

በኮቪድ 19 ወረርሽኝ አማካኝነት የሰዎችና የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ በተገደበበት ወቅትም እንዲሁ በሰሜን ሸዋ ጫጫ አካባቢ እያንዳንዱ አርሶ አደር ከአራት መቶ ኩንታል በላይ ካሮት አምርቶ ገዢ ያጣበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር።በዚህ ወቅትም የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ንግድ ሥራ በአካባቢው ተገኝቶ ምርቱን ወደ ማዕከላዊ ገበያ በማምጣት ለማህበረሰቡ ተደራሽ አድርጓል።ይህን የተመለከቱ ሌሎች ነጋዴዎችም ወደ አካባቢው በመግባት ምርቱ ሳይበላሽ ወደ ተጠቃሚው ማድረስ ችለዋል።በመሆኑም የታሰበውን ያህል ጉዳት በአርሶ አደሩ ላይ እንዳይደርስ በማድረግ የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፉ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

በቅርቡም አፋር ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የቲማቲም ምርት ተመርቶ በአካባቢው አንድ ኪሎ ቲማቲም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ በብር አምስት ብቻ ሲሸጥ ነበር።ይህንንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ወደ አካባቢው በመግባት የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፉ ምርቱን ማንሳት ችሏል።አምራቹ ለምርቱ ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ በአሁኑ ወቅት አፋር ላይ አንድ ኪሎ ቲማቲም ከ17 እስከ 20 ብር የሚሸጥበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።በመሆኑም የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ አምራቹን ከመደገፍ ባለፈ ለነዋሪዎች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን እየሠራ ይገኛል።



**ኢ**ትዮጵያ ውስጥ በብዛት ለብልሽት የሚጋለጡ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለመታደግ ኮርፖሬሽኑ 10 ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ በአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር የሚያስገነባው ህንጻ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል

**አዲስ ዘመን፦ የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፉ በዋነኝነት ምርቶቹን ተደራሽ የሚያደርገው ለየትኞቹ አካባቢዎችና የማህበረሰብ ክፍሎች ነው?**

**አቶ መህዲ፦** ዘርፉ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አራት ማከፋፈያዎችና 52 የሽያጭ መደብሮች አሉት።እነዚህ የሽያጭ መደብሮች የሚገኙትም በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ሲሆን፤ ከስድስት ኪሎ ጀምሮ እስከ አቃቂ እንዲሁም ከጦር ኃይሎች ወይም ከአየር ጤና አንስቶ እስከ ሲኤምሲ ሃያት አደባባይ ድረስ የመሸጫ ሱቆች ወይም ኮንቲነሮች አሉ።በአጠቃላይ በከተማዋ በሁሉም አካባቢዎች ማለት በሚቻል መልኩ በሚገኙት በእነዚህ ሱቆች አማካኝነት ህብረተሰቡ ማግኘት ይችላል።በእነዚህ የመሸጫ ሱቆችም መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው ተጠቃሚ የሚሆኑት።

**አዲስ ዘመን፦ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን እንዴት ነው የምታገኙት?**

**አቶ መህዲ፦** የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ከተመረቱባቸው አካባቢዎች የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም እናነሳለን።አንደኛው ከገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት፣ ከዩኒየኖች፣ ከኮሜርሻል ፋርሞችና በቀጥታ ከገበሬዎች ማሳ ላይ በመግዛት ምርቶቹን ሰብስበን፣ አከማችተንና አዘጋጅተን ለማህበረሰቡ ተደራሽ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፦ ዘርፉ ከአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ የሚያቀርባቸው ምርቶች ምንድናቸው? እሴት ጨምሮ በማቅረብ ረገድስ ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ መህዲ፦** የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ይበልጥ ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ በጥሬው ብቻ ሳይሆን ወደፊት እሴት ጨምሮ ለማቅረብ እየተሠራ ነው።የተለያዩ ሥራዎችን ለአገር በሚጠቅም መንገድ ለመሥራት ኮርፖሬሽኑ አቅዶ እየሠራቸው ከሚገኙ ሥራዎች መካከል አሽጎ ማቅረብ አንዱ ነው።

እሴት ጨምሮ ለገበያ ለማቅረብ ባለው እቅድ መሰረት ፍራፍሬና ስኳርን አሽጎ ለገበያ ማቅረብ የሚያስችሉ ማሸጊያ ማሽኖች ተተክለዋል።በመሆኑም ወደፊት ስኳርና ፍራፍሬዎች ከኢትፍሩት ማከፋፈያ ሱቆች በተጨማሪ በተለያዩ ሱፐርማርኬቶች ጭምር ታሽገው እንዲቀርቡ ይደረጋል።ይህም ዘርፉን በማሳደግ ይበልጥ ውጤታማ ሊያደርገው ይችላል።ኮርፖሬሽኑ በአስር ዓመት ውስጥ አሳካዋለሁ ብሎ ከያዛቸው ተግባራት መካከል በተለይም እሴት በመጨመር ረገድ የሚሠሩ የተለያዩ ሥራዎችን በሂደት ተግባራዊ የሚያደርግ ይሆናል።

ፍራፍሬዎች ሳይበላሹ ለብዙ ጊዜ መቆየት እንዲችሉ በማድረግ አሽጎ ለገበያ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት በሰዎች ጤና ላይ ጉዳት የማያደርሱ የተለያዩ ኬሚካሎች ማሸጊያው ላይ ይቀባሉ።ወደፊትም ምርቱ የሚታሸጉት እነዚህ ኬሚካሎች ተቀብተው ነው።ይህም የፓኬጁን ደረጃ በጠበቀ መንገድ የሚዘጋጅ ሲሆን፤ ምርቶቹም ከኢትፍሩት በተጨማሪ በሱቆችና በሱፐር ማርኬቶች ለገበያ የሚቀርቡ ይሆናል።ይህም እሴት በመጨመር ረገድ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚራምድ ነው።በአሁኑ ወቅትም ማሽኑ ተተክሎ አንዳንድ የማጠናቀቂያ ሥራዎች የሚቀሩ ሲሆን፤ በቀጣይም ቀሪ ሥራዎችን በማጠናቀቅ የፍራፍሬ ምርቶቹ ታሽገው ለገበያ የሚቀርቡ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፦ የዋጋ ግሽበትን ከመከላከልና ገበያን ከማረጋጋት አንጻር ያለው ሚናስ ምን ይመስላል?**

**አቶ መህዲ፦** የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ስራ ዘርፍ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች የሚያገለግል እንደመሆኑ የዋጋ ንረትን ከመከላከል አንጻር በተቻለ መጠን ገበያን ለማረጋጋት ይሰራል።የምርቶች ዋጋ የሚተመነውም እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ባገናዘበ መልኩ ነው።

ዘርፉ በገበያው ካለው የምርቶች ዋጋ እስከ 40 በመቶ የሚደርስ ቅናሽ አለው።አብዛኛው ምርት በዚህ መጠን ልዩነት ያለው በመሆኑ በተጠቃሚው ማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው ተቋም ነው።

በተለይም በአሁኑ ወቅት ባለው ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት ዘርፉ እስከ 40 በመቶ ልዩነት በመያዝ ከአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በተጨማሪ የተለያዩ የሰብል ምርቶችንም ጭምር ለማህበረሰቡ በማቅረብ ገበያን የማረጋጋት ሥራ ይሠራል።በመሆኑም ለአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ዘርፉ ተመራጭና ፋታ የሚሰጥ ሆኗል።በዚህ ረገድ በተለይም የኑሮ ውድነቱ በህብረተሰቡ ላይ ጫና እንዳያሳድር በማድረግ አንጻር አበርክቶው የጎላ እንደሆነ ይሰማናል።

ዘርፉ በኢትፍሩት መደብሮቹ አማካኝነት ለማህበረሰቡ እያሰራጫቸው ከሚገኘው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በተጨማሪ የተለያዩ የፍጆታ ዕቃዎችን በማቅረብ ለህብረተሰቡ ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።ለአብነትም የስኳር ምርትን ከስኳር ኮርፖሬሽን ተቀብሎ ለሆቴል፣ ለሬስቶራንት፣ ለካፌዎች፣ እንዲሁም የመንግሥት ተቋማት ለሆኑ ሆስፒታሎችና ለሌሎችም በማከፋፈል ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።በተመሳሳይ የዘይት ምርትንም እንዲሁ በኮርፖሬሽኑ አማካኝነት ከውጭ አገር በማስመጣት ለሸማቾችና ለመንግሥት ተቋማት ያከፋፍላል።

**አዲስ ዘመን፦ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በማስቀረትና በአገር ውስጥ በመተካት እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ ብልሽትን በመከላከል ረገድ ዘርፉ ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ መህዲ፦** ፍራፍሬን በሚመለከት በቅርቡ ለማስተዋወቅ የአፕል ምርትን ከውጭ ከሚያስገቡ አስመጪዎች በመቀበል የማከፋፈል ሥራ እየሠራ ነው።ይህም ለማስተዋወቅ ተብሎ በቅርቡ የተጀመረ ሥራ ሲሆን፤ ወደፊት ግን በጥናት የምናየው ይሆናል።ነገር ግን ዘርፉ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የአትክልት ዘሮችን ከውጭ አገር በማስመጣት ለአምራቾች ማለትም ለዩኒየኖች፣ ለህብረት ሥራ ማህበራትና ለሌሎች ኮሜርሻል ፋርሞች የማከፋፈል ሥራ ይሠራል።ይህም ከውጭ የሚገቡ የአትክልት ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚደረገውን ጥረት የሚያበረታታ ነው።

በአሁኑ ወቅትም የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ተግባራዊ ሊያደርገው የተዘጋጀው ባለማቀዝቀዣ መጋዘን ዘርፉን ውጤታማ ማድረግ እንደሚያስችል ይታመናል። በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት ለብልሽት የሚጋለጡ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለመታደግ ኮርፖሬሽኑ 10 ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ በአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር የሚስገነባው ህንጻ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።ምርቶቹ ሳይበላሹ ወደ ገበያ መድረስ እንዲችሉ ጉልህ አበርክቶ የሚኖረው ይህ ባለማቀዝቀዣ መጋዘን አትክልትና ፍራፍሬዎች ውድ በሆኑ ጊዜና ምርት በስፋት በሚገኝበት ወቅት በብዛት ገዝቶ ለማቆየት ያስችላል።የምርት እጥረት በሚፈጠርበት ወቅትም ምርቱን አውጥቶ ለማህበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የማድረግና ገበያን በማረጋጋት ረገድ አበርክቶው የጎላ ነው።

ከኤክስፖርት አንጻር እንዲሁ ጠቀሜታው የጎላ ነው፤ የአምራቾችን የፍራፍሬ ምርት ገዝቶ፣ አቆይቶ፣ አከማችቶና አዘጋጅቶ ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ለውጭ ገበያ እንዲደርስ በማድረግ ለአገሪቷ የውጭ ምንዛሪ እድገት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

**አዲስ ዘመን፦ በሀገራችን የአትክልትና ፍራፍሬ የብክነትና የብልሽት ምጣኔ ምን ያህል ነው?**

**አቶ መህዲ፦** አትክልትና ፍራፍሬ እየነገዱ ብክነትና ብልሽትን መቀነስ ይቻል ይሆናል እንጂ መቶ በመቶ ማስወገድ አይቻልም።ከዚህ አንጻር ዘርፉ በ40 ዓመት ቆይታው ምንም እንኳን የአትክልትና ፍራፍሬ ማቀዝቀዣ መጋዘኖችና መኪናዎች ባይኖሩትም ሠራተኛው በዘርፉ የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው በመሆኑ በተለይም ምርቶቹ ሲገቡ በምን አግባብ መግባት እንዳለባቸው፤ እና ሲወጡ እንዴት መውጣት አለባቸው በማለት የራሱን የአሰራር ዘዴ በመጠቀም የብክነትና የብልሽት መጠን ይቀንሳል።በመሆኑም የምርት ብልሽትና ብክነትን በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ መጥቷል።ከዚህ በተጨማሪም ኢትፍሩት ካይዘንን ተግባራዊ በማድረግ የምርት ብልሽትን በመቀነስ ረገድ ለውጥ ማምጣት ተችሏል።

ተቋሙ ስድስት በመቶ ያህሉን የአትክልትና ፍራፍሬ ብክነትን መቀነስ የቻለ ሲሆን፤ ብክነቱ በትነት መልክም የሚፈጠር እንደመሆኑ አትክልትና ፍራፍሬ ከፍተኛ እርጥበት በውስጣቸው የያዙ በመሆናቸው በትነት መልክ የሚፈጠር ብክነትን ሁለት በመቶ፤ ብልሽትን ደግሞ አራት በመቶ በድምሩ ስድስት በመቶ ብክነትንና ብልሽትን መከላከል ተችሏል።ከዚህ በተሻለ ለመከላከልም እየተሠራ ነው።ይህም እንደየአገራቱ ባህሪው የተለያየ መጠን ያለው ሲሆን እንደ አገር የኢትፍሩትን የብክነትና የብልሽት መጠን ብንመለከት አነስተኛ ነው ብለን ማለት እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፦ ለቃለ ምልልሱ ሳደረጉልን ትብብር በእጅጉ እናመሰግናለን!**

**አቶ መህዲ፦** እኔም አመሰግናለሁ!

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## በጎ ፍቃድ በዓላትና ክረምትን ለምን ይጠብቃል?

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ማህበራዊ ደህንነቱ የተረጋገጠ ሕዝብ ማህበራዊ ፍትህና ተጠቃሚነቱ ይበልጥ ይረጋገጣል። ማህበራዊ ችግሮቹም ተቀርፈው ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንደሚኖር ሁሉንም የሚያስማማ ሐቅ ነው። በመሆኑም ማህበራዊ ችግሮችን በመቅረፍ ማህበራዊ ደህንነትን በማረጋገጥ ሂደት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በሀገራችን ከጥንት አባቶቻችን ጀምሮ በቅብብሎሽ የመጣው የዜጎች የእርስ በእርስ መረዳዳት ባህል በጣም አስደሳችና ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው። ይህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንቅስቃሴ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ከተከሰተበት ጊዜ ይበልጥ ጎልቶ መውጣት እንደቻለ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

በኢትዮጵያ ቃላት በማይገልጸው የኑሮ ውድነትና የመኖሪያ ቤት እጦት ምክንያት እየተንገላታ ያለውን የሕዝብ ቁጥር ሆድ ይፍጀው። ምንም እንኳን አብዛኛው ዜጋ የዚህ ገፈት ቀማሽ ቢሆንም ችግሮቹን ለመቅረፍ መንግሥትም ይሁን መላው ሕዝብ የበጎ ፍቃድ ስራዎችን በዚህ ችግር ወቅት ከማድረግ ይልቅ የበዓላትና የክረምት ወቅትን ሲጠብቁ ነው የሚስተዋለው።

በዓላትን ጠብቀው በኑሮ የተጎሳቆሉ እናቶችንና አቅመ ደካሞችን ከተለያዩ ስፍራዎች በመሰብሰብ ጥቁር መነፅር አድርጎ ከፊት ለፊት ካሜራ ደቅኖ ዘይትና ዱቄት ማደል በሀገራችን የተለመደ ተግባር ነው። የመስጠት መጥፎ የለውም ይሁን። እኔን ‹‹አጃኢብ›› የሚያሰኘኝ ነገር ግን ከመስጠቱ ጀርባ ለሳምንት የማይሆን ሽቀጥ ድጋፍ ለማድረግ የሚዲያዎች ጋጋታና የሚደረጉ ቃለመጠይቆች በተረጂዎቹ ሥነ ልቦና ላይ ምን አይነት ጫና ሊያሳድር እንደሚችል ማሰቡ ነው።

ለሌላው መርዳት መልካም ስራ ሆኖ ሳለ የካሜራ ጋጋታና ተረጂ ዜጎችን ቃለ መጠይቅ ማድረጉ ለምን እንዳስፈለገ አይገባኝም። እግዜሩም ቢሆን የሚደረጉ መልካም ተግባራት ለፅድቅ እንጂ ለካሜራ እይታ ሲሆን ደስ የሚለው አይመስለኝም። የምታደርጉትን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በልባችሁና ከካሜራ ጀርባ ቢሆን እንዴት ጥሩ ይሆን ነበር ብዬ አሰብኩኝ፤ እናንተም ሀሳቤን እንደምትጋሩ እምነቴ ነው። ሕይወታችን የካሜራ ሰለባ እንደሆነ ይሰማኛል። በየማህበራዊ ትስስር ገፃችን የምንለጥፈው ፎቶግራፍ እና በገሀዱ ዓለም ኑሯችን የተለያየ መሆኑ የሚታወሰኝ የሚያምር ህንፃና አረንጓዴ ስፍራዎችን ስናገኝ ያለማንገራገር ፎቶ ስንነሳ ነው።

ወደ ጉዳዬ ስመለስ፤ እነዚህን ዜጎች በዓል በመጣ ቁጥር ሽቀጥ ከማደል ይልቅ በቋሚነት ስራዎችን በመስራት ከራሳቸው አልፎ ለቤተሰቦቻቸው የሚተርፉበትን እድል በማመቻቸት የመንግስትም ይሁን የግለሰቦችን እጅ እንዳይጠብቁ ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። በዓል ሲመጣ እርዳታ ማድረጉ በጣም የሚያስመሰግን ነው፤ ዳሩ ግን ለታይታ የምንጥረውን ያህል ከችግር የሚወጡበትን መንገድ ለማመቻቸት ብንሰራ ለተረጂዎችም ለአገርም የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።

ክረምት ሲመጣ አካፋና ዶማ ይዞ ያረጁ ቤቶችን የማደስ ስራ ለምን ዘወትር እንደማይካሄድ ሌላኛው ጥያቄዬ ነው። ለዚህ ተግባር ከክረምት ይልቅ በጋ የተሻለ እንደሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም የሚታደስላቸው ዜጎች አይቸገሩም።

ሕዝቡ የበጎ ፍቃድ ስራዎች ላይ ያለው ተሳትፎ የሚበረታታ ቢሆንም፤ ታዲያ ይሄንን በተደራጀ መልኩ የሚያሰራ የመንግስት ተቋምም ሆነ የሲቪል ማህበራት እንደሚያስፈልጉ ሳይታለም የተፈታ ነው።

አገራችን እያራመደችው ያለውን የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ስኬታማ ለማድረግ እንዲቻል በጎ ፈቃደኛ ዜጎች በአካባቢ ልማት፣ በችግኝ ማፍላትና ተከላ፣ በደን ልማት፣ ሀገር በቀል ዝርያዎችን በማፍላትና በመትከል ሂደት ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉና በኢኮኖሚ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት የአደጋ ስጋትና ተጋላጭነትን ለመቋቋም ያላቸው አቅም ውስን በመሆኑ ለከፋ ችግርና ቀውስ ሲጋለጡ ይስተዋላል። በመሆኑም የአደጋ ተጋላጭነትንና ችግርን በዘላቂነት ለመቅረፍ በሚከናወነው ስራ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጉልህ ሚና አለው።

በጎ ፈቃደኛ ዜጎች በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች በመደገፍና መልሶ በማቋቋም፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስና በመገንባት፣ ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን በመንከባከብ፣ አካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን በመንከባከብ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችንና ሌሎች ተጋላጭ ዜጎችን መርዳትና መደገፍ አለባቸው።

ሰላም ልማትና ዕድገት በቀላሉ ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ ለዘላቂ ሰላም መስፈን የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ርብርብ በተለይም ደግሞ የወጣቱ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን በአግባቡ በመጠቀም ለሀገር ግንባታ ልናውል እንደሚገባ አምናለሁ፤ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዜጎች በአዎንታዊ አስተሳሰብ ስብዕናቸው እንዲገነባ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በዚህ መንገድ ያለፉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሻለ ስብዕና ኖሯቸው ስለሰውና ስለሀገር እንዲያስቡ ያስችላል። በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚከናወኑ ተግባራት ለሀገር ከሚሰጡት ጠቀሜታ ባሻገር በገንዘብ ቢተመን መንግስት ሊያወጣ የሚችለውን ከፍተኛ ወጪ ማዳን እየተቻለ እንደሆነ ግልፅ ነው።

ወጣቶች የበጎ አድራጎት ስራዎችን በሚያከናውኑበት ጊዜ እውቀት፣ ባህል፣ በአንድነትና በፍቅር አብሮ የመኖር እሴቶችን ከማህበረሰቡ ያገኛሉ። አንድ ዜጋ ደም በሚለግስበት ወቅት የሱ ደም ዘርና ጎሳን ሳይለይ የሰው ፍጥረትን ይታደጋል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን በአግባቡ ከተጠቀምንበት እድሜ፣ ጾታ፣ ብሔር፣ ፖለቲካና ኃይማኖት ሳይገድባቸው ዜጎች ጥላቻንና ቁርሾን በመተው የሚሳተፉበትና ለሀገር ግንባታ ያለው ሚና ትልቅ በመሆኑ ህብረተሰቡ ስለ በጎ ፍቃድ አገልግሎት ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ ሚዲያዎችና ሁሉም ባለ ድርሻ አካል ሊረባረብ የሚገባው ጊዜና ወቅት ጠብቆ መሆን የለበትም።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን በተደራጀ መልኩ ለማስቀጠል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተለያዩ የበጎ ፍቃድ ህብረቶችን በመፍጠር በሌላው የዓለም ክፍል ላይ ያሉትን መልካም ተግባራት ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋትና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲ በማዘጋጀት ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራበት ብዙ ጥያቄዎች ምላሽ እንደሚያገኙ እሙን ነው።

# ዓለም አቀፍ



## ፕሬዚዳንት ፑቲን አገራቸው ከአፍሪካ ጋር ላላት ግንኙነት ቅድሚያ እንደምትሰጥ አስታወቁ

በሩሲያና በዩክሬን ጦርነት ምክንያት ከምዕራቡ ዓለም ማዕቀብ የተጣለባቸው የሩስያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን አገራቸው ከአፍሪካ ጋር ላላት ግንኙነት ቅድሚያ ትሰጣለች። “አገራችን ከአፍሪካ አገራት ጋር ለመተባበር ቅድሚያ እንደምትሰጥ እና በዚህም እንደምትቀጥል አጽንኦት መስጠት እፈልጋለሁ” ሲሉም ፕሬዚዳንት ፑቲን ትናንት ሰኞ ሞስኮ በተካሄደው የሩሲያ-አፍሪካ ጉባኤ ላይ ተናግረዋል።

ከዩክሬን በሚቀርበው እህል ላይ የተደረሰው ስምምነት ካልታደሰ ሩሲያ ለተቸገሩ የአፍሪካ አገራት በነጻ እህል እንደምታቀርብም ነው ፑቲን ቃል የገቡት። “በባለፉት ዓመታት ሲላክ የነበረውን የእህል መጠን ለአፍሪካ አገራት በተለይም ከሩሲያ ለሚፈልጉ በነጻ ለማቅረብ ዝግጁ ነን” ሲሉ መናገራቸውን የሩሲያ የዜና ወኪል ታስ ዘግቧል።

ፕሬዚዳንት ፑቲን ሩሲያ የደረሰችባቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለአፍሪካ አገራት እንደምታካፍል እና የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያመርቱ የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥልም ተናግረዋል። ሩሲያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአፍሪካ ተጽእኖዋን እያሰፋች የምትገኝ ሲሆን “ አህጉሪቱ እያቆጠቆጠ ባለው የብዝሀ የዓለም ስርዓት ላይ ስልጣኗን እና ሚናዋን ማሳደግ እንደምትቀጥል አምናለሁ” ብለዋል።

በጉባኤው ላይ ከ40 በላይ የአፍሪካ አገራት ልዑካን እየተሳተፉ መሆኑንም የክሬምሊን የፕሬስ አገልግሎት ዘግቧል። በመጪው ሰኔ ወር ላይ ሁለተኛው የሩሲያ-አፍሪካ ጉባኤ የሚካሄድ ሲሆን ፕሬዝዳንቱ የአፍሪካ መሪዎችን እንደሚቀበሉ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## ትራምፕ ሊታሰሩ ይችሉበታል በተባለው ቀን የአሜሪካ ፖሊስ በተጠንቀቅ ላይ ነው



የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ እየተደረገባቸው ካለው ምርመራ ጋር ተያይዞ በዚህ ሳምንት የሚታሰሩ ከሆነ ሊፈጠር የሚችለውን አለመረጋጋት ለመቆጣጠር በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች ፖሊስ ዝግጅቱን እያደረገ መሆኑ ተሰምቷል።

ባለስልጣናት በኒውዮርክ፣ ዋሽንግተን ዲሲና ሎስአንጀለስ ከተሞች የተሰማራው የፖሊስ ኃይልን አጠናክረዋል። የማንሃታን ጠቅላይ አቃቤ ህግ ትራምፕ ከአንዲት የወሲብ ፊልም ተዋናይት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለመደበቅ ገንዘብ ከፍለዋታል የሚል ክስ ሊመሰርት ይችላል። ይህ የሚሆን ከሆነ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ለነበረ ሰው በዚህ አይነቱ የወንጀል ጉዳይ ሲከሰስ የመጀመሪያው ይሆናል።

የትራምፕ ጉዳይ ሊታይ ይችላል በተባለበት የማንሃታን ፍርድ ቤት አካባቢ ከትላንት ወዲያ ሰኞ የብረት ማገጃዎች ተተክለዋል። የአሜሪካ መገናኛ ብዙኃን በስፋት ግምታቸውን እንዳስቀመጡት ከሆነ በፍርድ ቤቱ ትራምፕ ክስ ሊመሰረትባቸው፣ የጣት አሻራ ሊሰጡበትና ፎቶግራፍ ሊነሱበት ይችላሉ። በከተማው በሚገኘው ትራምፕ ታወር አቅራቢያም የተሰማራው የፖሊስ ቁጥር ከወትሮው ጨምሮ ታይቷል።

የሲቪል ልብስ የሚለብሱ መርማሪዎችን ጨምሮ ሁሉም የኒውዮርክ ፖሊስ ክፍል አባላት ትናንት ማክሰኞ የደንብ ልብሳቸውን እንዲለብሱ እና ለግዳጅ በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ትዕዛዝ እንደተሰጣቸው የቢቢሲ ምንጮች ተናግረዋል። የኒውዮርክ ፖሊስና ኤፍቢአይ የጋራ ጸረ ሽብር ኃይል ከቀድሞና የወቅቱን ፕሬዝዳንት የመጠበቅ ተልዕኮ ካለው የአሜሪካ ሚስጥራዊ አገልግሎት ጋር ትራምፕ ሊታሰሩ ስለሚችሉበት ሁኔታ መምከራቸው ተሰምቷል። በዋሽንግተን የሚገኘው እና ህግ አውጪዎችን የሚጠብቀው የካፒቶል ፖሊስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ዛሬ ማክሰኞ ሊያውጅ እንደሚችል ምንጮች ለአሜሪካው ሲቢኤስ ተናግረዋል። የተሰጠው ትዕዛዝ ከሌሎች የህግ አስከባሪዎች ጋር ያለውን ትብብር ለማጠናከር ያለመ ነው። ሌሎችም የጸጥታ ኃይሎች በተጠንቀቅ ሊቆሙ እንደሚችሉም ተነግሯል።

በሎስአንጀለስ የግዛቱና የፌዴራል የጸጥታ ኃይሎች የትራምፕ ደጋፊዎች የሚያደርጉትን ተቃውሞ ለመከላከል መዘጋጀታቸው ተዘግቧል። ባለፈው ቅዳሜ ትራምፕ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ማክሰኞ ልታሰር እችላለሁ ብለው መጻፋቸውን ተከትሎ የአሜሪካ የህግና አስተዳደር ባለስልጣናት እየተሰነዘረ ያለውን ዛቻ የአሜሪካ የደህንነት ተቋም እየመረመረ ይገኛል።

አብዛኛው ዛቻ ያነጣጠረው ትራምፕ ላይ ክስ እንደሚመሰርቱ በሚጠበቁት የማንሃታን አውራጃ ጠቅላይ አቃቤ ህግ አሊቪን ባራግ ላይ ነው። ጠቅላይ አቃቤ ህጉ ለሰራተኞቻቸው በኢሜይል በላኩት መልዕክት ትራምፕ በተመሳሳይ ቀን ደጋፊዎቻቸው መቃውም እንዳለባቸው መጻፋቸውን ገልጸዋል። “በመኮንኖቻችን ላይ ዛቻ ወይም ወከባ የማድረስ ሙከራን አንታገስም” ሲሉም ጽፈዋል።

ጠቅላይ አቃቤ ህጉ ትራምፕ ላይ ክስ ለመመስረት በቂ ማስረጃ መኖሩን የሚመረምር የዳኞች ቡድን አቋቁመዋል። ጉዳዩም ትራምፕ ስቶርሚይ ዳኒልስ ከተባለች የወሲብ ፊልም ተዋናይት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመደበቅ 130 ሺህ ዶላር ከፍለዋል መባሉ ላይ የሚያጠንጥን መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

**ማህበራዊ**

# ባለውለታዎቻችን

## «የምድራችን ጀግና!»ሎሬት ዶክተር ተወልደብርሃን ገብረእግዚአብሔር ሲታወሱ

**እፀገነት አክሲሱ**

ዶክተር ተወልደ ብርሃን በትግራይ ክልል በአድዋ ከተማ አቅራቢያ ባለች የገጠር መንደር እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር የካቲት 19 ቀን 1940 ዓ.ም ነው የተወለዱት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በንግስተ ሳባ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከጥቅምት 1951 እስከ ሰኔ 1955 ተከታትለዋል። ከዚያም ወደ ጀኔራል ዊንጌት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማምራት በ1959 በከፍተኛ ውጤት ወደ ቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በስነ ህይወት ትምህርት ክፍል በ1963 ዓ.ም ከተመረቁ ተማሪዎች የወርቅ ሜዳልያን በማጥለቅ በከፍተኛ ማዕረግ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። ከዚያም ወደ እንግሊዝ አገር አቅንተው የዶክትሬት ዲግሬአቸውን ከዌልስ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል።

በረዳት መምህርነት ስራቸውን በ1963 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሃዱ ያሉት ዶክተር ተወልደብርሃን በትምህርት ክፍል ኃላፊነት ፤ በዲንነት ፤ በዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትነት እና በሚኒስትርነት ሰርተዋል። 18 በሚሆኑ ዓለም አቀፍ የብዝሃ ህይወት እና አካባቢ ጥበቃ ተቋማት ከክብር አባልነት እስከ አመራርነት አገልግለዋል። 38 የሚሆኑ የምርምር ስራዎችን በዓለም አቀፍ የህትመት የዕውቀት መድብሎች በማሳተም አንቱ የተሰኙ ሰው ናቸው።

ሽልማቶቻቸው እስከ የዓለም ኖቤልን የሚተኩ የፈረንሳይ ልዩ የዜግነት ክብርን የሚያቀዳጁትን የሚጨመሩ ናቸው። ባላቸው ልዩ ችሎት እና በውጭ አገራት አሰራር ሁለተኛ ዲግሪ /ማስተርሳቸውን/ አልተማሩም በቀጥታ ከመጀመሪያ ዲግሪ በሶስት ዓመታት ውስጥ ዶክትሬታቸውን አግኝተዋል። ዶክተር ተወልደ በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ ፋኩልቲ ዲን ሆነው አገልግለዋል። ከ1975 እስከ 1983 በነበረው ዘመን ደግሞ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሆነው ሰርተዋል። አስመራ በህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዕቢያ) ስትከበብ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በያኔው ካቢኔ ውስጥ የባህል ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል። የደርግ መንግሥት ከተወገደ በኋላም ለብዙ ዓመታት በሚታወቁበት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተርነት ሰርተዋል።

የአካባቢ እና ደን ሚኒስቴርን በማዋቀር ስለአረንጓዴ ልማት 53 የአፍሪካ ሀገራት ቁመው እንዲሟገቱላቸው ፈርመው የወከሏቸው ብቸኛ የአረንጓዴ አብዮት መድረክ ተቆርቋሪ እና ተከራካሪ ናቸው። በስራዎቻቸውም በአካባቢ ጥበቃ ዋና ባለስልጣን በመሆን ከመጋቢት 1995 እስከ 2016 ድረስ በከፍተኛ ኃላፊነት በመስራት እና በዚህ ዓመት በጡረታ በገዛ ፈቃዳቸው ከመስሪያ ቤቱ ተሰናብተዋል። ከነሐሴ 1983-ግንቦት 1991 ዓ.ም ድረስ አስመራ ዩኒቨርሲቲን በፕሬዚዳትነት በመምራት የያኔዋን ክፈለ ሀገራዊት ኤርትራ የዕውቀት በራፎች ላይ ታሪክ ፅፈዋል።

የስነ ህይወት ልህቅናቸው ከዓለም መድረክ ተጠሪነት እስከ ስትራቴጂ አርቃቂነት ይመራናል። ዶክተር ተወልደብርሃን ገብረእግዚአብሔር የእጽዋት ጄኔቲክ ሃብት ለንግድ ሲባል እንዳይለወጥና በተለይ ሰለጠኑ የሚባሉት አገሮች የገበሬው ሕብረተሰብ ለዘመናት ጠብቆ ያቆየውን እንዲያከብሩ ተከራክረዋል። ይህ መብት እንዲከበርና የእጽዋትን ጂን እየቀየሩ በፓተንት በመጠበቅ ችግር እንዳይፈጥሩ አስተባብረዋል።

ዶክተር ተወልደብርሃን በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ላደረጉት ምርምርና በጉዳዩ ዙሪያ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲፈጠር ላደረጉት ጥረት በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2000 ሚሊንየም ዓለም አቀፉን የአቋራጭ ኖቤል ሽልማት (በትክክለኛ ስሙ Right Livlihood Award የሚባለውን) ተሸልመዋል;; በእዚህ መስክ ይህ ሽልማት ለዶክተር መላኩ ወረደ ከመሰጠቱ ሌላ በእንዶድ ምርምር ላደረጉት ዶክተር አክሊሉ ለማ እና ዶክተር ለገሠ ወልደ ዮሓንስ ተሸልመዋል። ይህ የዕውቅና ሽልማት የኖቤል ሽልማት በማይሰጥበት መስክ ስለሆነ አማራጭ ነው ይባላል።

ዶክተር ተወልደ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ 2006 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች የሚሸልመውን Champions of the Earth ሽልማት አግኝተዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በ1997 የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቶአቸዋል።

እኚህ ሰው የአገራችንን የብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት ከማቋቋማቸውም በላይ ዝርያቸው ለመጥፋት የተቃረቡ አገር በቀል ዛፎችን በሰፊው በማጥናት ለዘራቸው ጥበቃ የሚደረግበት የኢትዮጵያ ጄኔቲክ ባንክ እንዲመሰረት ከፍተኛ ሚና ተወጥተዋል። የአገራችንን የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ የቀየሱትም እርሳቸው ናቸው። በተጨማሪም ዶክተር ተወልደ የአፍሪቃ አገራት የአሜሪካና የአውሮፓ ኩባንያዎች ወደ ከባቢ አየር በሚለቋቸው በካይ ጋዞች ለሚደርስባቸው ጉዳት ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ እንዲጠይቁ ካስተባበሩ መሪዎች አንዱ ናቸው።

ድምጻቸውን ከኢትዮጵያ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአፍሪካ አገሮችን ጨምሮ ቡድን ሰባት እና ቻይና ተብሎ የሚታወቀው የበርካታ አገሮች ስብስብ አፈ ቀላጤ ሆነው ሰርተዋል። የደኅንነተ-ሕይወት ዋና ተደራዳሪ ሆነው ለአርሶ አደርና አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች የሕያዋን ባለቤትነት መብትና አዛላቂ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ጉዳይ ዙሪያ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተከራክረዋል።

በይፋም ባይሆን ውስጥ ውስጡን የሦስተኛው ዓለም ክፍል ሰዎች (ምንም ቢማሩ) የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ረቂ የሆነ የመደራደሪያ ሃሳብ አያቀርቡም የሚል እብሪት በበለጸጉት አገሮች ተደራዳሪዎች ዘንድ ነበረና በዶክተር ተወልደ ዋና መሪነት ይቀርብ የነበረው የድርድር ሃሳብ ይዘትን በኃይለ ሃሳብ መምታት ሳይችሉ ሲቀሩ ሌላ ሞራል የሚነካ የሚመስላቸው ነገር ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ በአንድ የድርድር ዙር ላይ በእሳቸው ቡድን የሚቀርበው ሃሳብ አረንጓዴ ሰላም በተሰኘ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ጉዳይ አቀንቃኝ ድርጅት ተሰርቶ የተሰጣቸው እንጂ የራሳቸው እንዳልሆነ (ለማዘጋጀት ብቃቱ አይኖራቸውም ከሚል ንቀት) ሲነገራቸው እጅግ የተበሳጩበት ሁኔታ እንደ ነበር ስዊድን ሄደው የተናገሩትን ማስታወስ በቂ ነው። ድርድሮች በተወሰነ ጊዜ መቋጨት ያለባቸው ጉዳዮች ተይዞ ስለሆነ የሚጀመረው ብዙ ጊዜ የጊዜ እጥረት ስለሚያጋጥም ቀን ከሌሊት መደራደርን ይጠይቃል። ያደጉት አገሮች ብዙ ተደራዳሪዎች ይዘው ስለሚሄዱ የተወሰነው ሲደራደር ሌላው ያርፋል (እስከ መተኛት ድረስ)። እኛንና መሰለ አገሮችን ወክለው የሚሄዱት እነ ዶክተር ተወልደ ግን በስልሳ ዓመታቸው (በዛን ወቅት) በዛ ላይ የአስም በሽተኛ ሆነው ሌት ተቀን ከጎረምሶቹ ጋር ይደራደሩ በነበረበት ሁኔታ ነው የእብሪት ንግግሩንም ይሸከሙ የነበረው። እናም በሳቸው አባባል ምንም እንኳን ሰው ለመምታት ለመጨረሻ ጊዜ እጃቸውን ያነሱት የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ የነበሩ ጊዜ ቢሆንም ሞራል-ነኪ የሆነው የ'ብቃት-የላችሁም' አባባል ግን ሊቋቋሙት ስላልቻሉ 'ለመማታት' ተጋብዘው ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከምዕራቡ ዓለም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጽእኖ ይደረግባቸው የነበረ ከመድርከም ውጪ በሆነ ሁኔታ ነበር። የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም እርዳታ ጉዳይ እሳቸውን ዝም ከማሰኘት ጋር አቆራኝተው እያቀረቡ የሚያመጥቡት ጊዜና ሁኔታም ነበር። የግብርና ሚኒስትር ባለሥልጣናት በኩልም ሳይቀር 'ለምን አትተውም' ተብለው እንደነበር ተነግሯል። ያልተወደደላቸው አቋም በጥናተ ስረት ምህንድስና መሰረት የሚፈበረኩ ልውጥ ሕያዋን ከአንድ ዙር በላይ ተዘርተው የማይበቅሉ የሰብል ዘሮች ስርጭት በተመለከተ ያላቸው አቋም አንዱ ነበር። በሕያዋን ፍጥረቶች (ለምሳሌ ሰብሎችና ሌሎች እጽዋቶች) የባለቤትነት (ከባለአእምሮ ንብረትነት ጋር በተያያዘ) የምዕራቡ ዓለም አገሮች በትልልቅ አትራፊ ኩባንያዎች ግፊት የሚያራምዱት አደገኛ አቋም በመቃወምና ሌሎች በርካታ አገሮችንና ስብስቦችን በማስተባበር የትም እንዳይደርስ ለማድረግ የወሰዱት እርምጃ ሌላው ነው። የእሳቸው አቋም የነዚህ ሕያዋን ባለቤትና ዋና ተጠቃሚ እታች ያለው የማኅበረሰቡ ክፍል - ገበሬው - ነው የሚል ነው።

ተራ ወደ ሆነና ስብሰባ እንዳይሳተፉ ለማድረግ ቪዛ ወደመከልከል አካሄድም ተሞክሮ ነበር - በካናዳ። የዛሬ ሰባት ዓመት ነው። የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ በካናዳ ሞንትሬያል ከተማ ይካሄድ ነበር። ሞንትሬያል የተመድ ብዝኃ ሕይወት ጽህፈት ቤት መቀመጫ ነች። የዶክተር ተወልደ አቋም በካናዳ መንግሥት ዘንድ ያልተወደደ ስለነበር ቪዛ በማገድ ከስብስባ ሊያስቀራቸው ሞከረ። ብዙ ዓለም አቀፍ መጠየቂያዎች ተሞልተው የበርካታ አገር ምሁራን ካናዳውያንን ጨምሮ - ተቃውሟቸውን አሰሙ - ቪዛውም እንደገና እንዲያገኙ ተደረገ። ቪዛውን ካገኙ በኋላ የሚከተለውን ኢ-ሜይል ለደጋፊዎቻቸው ልከው ነበር።

**የ**ተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ በካናዳ ሞንትሬያል ከተማ ይካሄድ ነበር። ሞንትሬያል የተመድ ብዝኃ ሕይወት ጽህፈት ቤት መቀመጫ ነች። የዶክተር ተወልደ አቋም በካናዳ መንግሥት ዘንድ ያልተወደደ ስለነበር ቪዛ በማገድ ከስብስባ ሊያስቀራቸው ሞከረ። ብዙ ዓስም አቀፍ መጠየቂያዎች ተሞልተው የበርካታ አገር ምሁራን ካናዳውያንን ጨምሮ ተቃውሟቸውን አሰሙ

### ውድ ጓደኞቼ

ዛሬ ሜይ 24 ነው። ወደ አመሻሹ። ወደ ካናዳ ለመግባት እነሆ ቪዛዬን አግኝቻለሁ። ስለዚህ ብዙዎቻችሁን ሞንትሬያል አገኛችኋለሁ። የጉዞ ዝግጅቶቼ ሁሉ እንደታቀዱት ከተሳኩ ሜይ 26 ማታ ላይ ሞንትሬያል እደርሳለሁ። ጉዳትና ካሳ ላይ የሚያተኩረው የመጨረሻው ቀን ላይ እቀላቀላችኋለሁ። የወደፊቱ ዓለም አቀፍ የጉዳትና ካሳ ጉዳይ ላይ የሚኖረን አካሄድ ቅርጽ ለሁላችሁም በሚታይበት ደረጃ ላይ ሲሆን እደርሳለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ስቀላቀላችሁ በተሻለ ደረጃ የሚታይበት ሁኔታ ለመፍጠር የቻልኩትን በማድረግ እረዳለሁ። ከዚህ ስብሰባ በኋላ በአንድ ወይም በሁለት ስብሰባዎች አሰራሩን በጽኑ መሰረት ላይ አቁመን ኃላፊነት ከጎደለው የህያውን ምህንድስና እንዲታደገን እናደርጋለን የሚል ተስፋ አለኝ።

ስለ ትልቅ ድጋፋችሁ ሁላችሁንም አመሰግናለሁ። ብዙ አገሮችን ለአንድ ዓላማ እንዲሰሩ የማድረግ ዘይቤ በመንግሥት ደረጃ ሌላ ምት አስተናግዷል። ነገር ግን በማኅበረሰቦች ስብስብ ደረጃ ያለውና እናንተ አካል የሆናችሁበት አብሮ የመስራት ኃይል አሸናፊ ሆኗል። መንግሥታዊ እብሪትን ለመቆጣጠር ምናልባት በማኅበረሰቦች ስብስብ ደረጃ ያለው አብሮ የመስራት ሂደት ይዘን መግፋት አለብን። እስቲ አስቡበት። እኔም አስብበታለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ እመለሳለሁ።


**የማኅበረሰብ ሉሳዊነት ለዘላለም ይኑር!**
**በጣም አመስጋኙ ጓደኛችሁ**
**ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር**

በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ላደረጉት ምርምር እና በጉዳዩ ዙሪያ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲፈጠር ላደረጉት ዓለም አቀፍ አስተዋጽኦዎች በ1993 ዓ.ም የአማራጭ ኖቤል ሽልማት ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የሎሬትነት ማዕረግን አግኝተዋል። በ1998 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ መርሐ ግብር (ዩኔፕ) "የምድራችን ጀግና" ሲል በድጋሚ የሎሬት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል። በ2000 ዓ.ም "ዘ ጋርዲያን" የተባለ ዕድሜ ጠገብ ጋዜጣ "የፕላኔታችን ደህንነትን የጠበቁ ምርጥ 50 ሰዎች" ሲል ከጠቀሳቸው ሰዎች አንዱ ታላቅ ሳይንቲስት ብሏቸዋል። one world award' እና 'Organic International' ከተባለ ተቋም ጋር በመተባበር የህይወት ዘመን ተሸላሚ መሆን የቻሉም ሰው ናቸው።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1996 ዓ.ም ለአካባቢ ጥበቃ ተቆርቋሪው እና ተከራካሪው ዶክተር ተወልደብርሃን የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷዋል። ደራሲ ዘነበ ወላ "የምድራችን ጀግና" በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ከሽልማቶች ሁሉ ይህን እንደሚወደው ነግሮኛል ያለ ሲሆን ምክንያቱንም ሲገልጽ በአብሮ አደጎቼ ዕውቅና ሲሰጠኝ ደስ ይለኛል ማለታቸውን አስፍሯል። ዶክተር ተወልደብርሃን ከበጎ ሰው ሽልማት በተጨማሪ በአትዮጵያ ሚሊንየም የአካባቢ ተቆርቋሪ መድረክ የተሰኘ ተቋም 'የአረንጓዴ ጀግና' በሚል በብሔራዊ ቤተመንግስት የክብር ሽልማት ሰጥቷቸዋል።

የ82 ዓመቱ ዕድሜ ባለጸጋ ሳይንቲስት ዶክተር ተወልደብርሃን በህይወት ዘመናቸው ለአገራቸው ያበረከቱት አስተዋጽኦ አበርክቷቸው እና አርዓያነታቸው በጉልህ ቀለም ከሚጻፍላቸው ጀግና ኢትዮጵያውያን ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይቀመጣሉ።

ዶክተር ተወልደ ብርሃን የተመድ የአካባቢ ፕሮግራም የ2006 ሻምፒዮንስ ኦፍ ዘኧርዝ አሸናፊ ሲሆኑ የዓለም የወደፊት ምክር ቤትም አባል ናቸው። እኚህ የምድራችን ጀግና ለአገራቸው ለአህጉራቸው አንዲሁም ለዓለም በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ በርካታ ምርምርና በጉዳዩ ዙሪያ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲፈጠር በማድረግ የኢትዮጵያ ድንቅ ልጅ ስሟንም በዓለም መድረክ ከፍ አድርገው ያስተጋቡ ነበሩ:: ዶክተር ተወልደ ብርሃን በተወለዱ በ83 ዓመታቸው መጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል:: እኚህ ደንቅ ሰው የሶስት ልጆች አባትም ነበሩ።



# ስፖርት

## «ፍላጎታችን የ2023ቱን የአፍሪካ ዋንጫ መቀላቀል ነው»

- አሰልጣኝ ውበቱ አባተ

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) ለ2023 የኮትዲቯር አፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የምድባቸውን ሶስተኛና አራተኛ ማጣሪያ ጨዋታ ከጊኒ ጋር መጋቢት 15 እና 18 ያከናውናሉ። ለዚህም አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ከሳምንት በፊት ለሃያ ሶስት ተጫዋቾች ጥሪ በማድረግ ዝግጅታቸውን በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ስቴድየም ሲያከናውኑ መቆየታቸው የሚታወቅ ሲሆን ከርዋንዳ ብሔራዊ ቡድን ጋር ያደረጉትን የአቋም መለኪያ ጨዋታም አንድ ለምንም አሸንፈዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከትናንት በስቲያ ምሽት ሁለቱን ፍልሚያዎች ወደሚያደርግበት ሞሮኮ የተጓዘ ሲሆን፣ ከጉዞው ቀደም ብሎም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ሥራ-አስፈፃሚ አቶ ባህሩ ጥላሁንና አሠልጣኝ ውበቱ አባተ መግለጫ ሰጥተዋል።

ዋልያዎቹ ከጊኒ ጋር ለሚያደርጉት የደርሶ መልስ ጨዋታ ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ አድርገው ከመጋቢት 6 ጀምሮ ሲዘጋጁ መቆየታቸውን ያስታወሱት አሰልጣኝ ውበቱ፣ በህመም እና በክለብ ግዴታ ምክንያት ያልተገኙ ተጫዋቾች ቡድኑን እንዳልተቀላቀሉ ተናግረዋል። አቡበከር ናስር በጉዳት፣ ይገዙ ቦጋለ ደግሞ አንድ ቀን ከቡድኑ ጋር ልምምድ ሰርቶ የጉልበት ጉዳት በማስተናገዱ ከስብስባቸው ውጭ መሆኑን ጠቁመዋል። በሁለቱ ተጫዋቾች ምትክም ለቡድኑ አዲስ ያልሆኑ ተጫዋቾችን እንደጠሩ አብራርተዋል። ቡድኑ የ4 ቀን ልምምድ ተሞክሮ ከዚህ በፊት እንዳልነበረው የገለፁት አሰልጣኙ፣ በርዋንዳው የአቋም መለኪያ ጨዋታ ላይ ቡድናቸው ጥሩ ነገር ማሳየቱን ተናግረዋል።

"በዋናነት ፍላጎታችን የ2023ቱን የአፍሪካ ዋንጫ መቀላቀል ነው። ለዚህ ደግሞ የጊኒው የደርሶ መልስ ጨዋታ ወሳኝ ነው። በዚህም ከጨዋታዎቹ የበለጠውን ነጥብ ለማግኘት እንጥራለን። 6 ነጥብ መሪነታችንን ያስቀጥላል ፤ ቢያንስ ግን 4 ነጥብ ለማሳካት ነው ጨዋታዎቹን የምናደርገው" ያሉት አሰልጣኝ ውበቱ፣ በስብስቡ ውስጥ የሚገኙት ተጫዋቾች በጥሩ ተነሳሽነት ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

ከጊኒ ብሔራዊ ቡድን አጨዋወት ጋር በተገናኘ በተለይ ከቆሙ ኳሶች እና ተሻጋሪ ኳሶች ጋር ተያይዞ ቡድኑ ዝግጅት እያደረገ እንደሆነና የተጋጣሚ ቡድን የተካነበትን የአጨዋወት መንገድ ማጥፋት ስለማይቻል በተቻለ መጠን ለመቀነስ እየተዘጋጁም አሰልጣኙ አመላክተዋል። ከዚህ ውጪ በልምምድ ወቅት መጠነኛ ጉዳት ያስተናገደው ረመዳን የሱፍ ጉዳቱ ለከፋ እንደማይሰጠው አክለዋል።

የዋልያዎቹ ተጋጣሚ ጊኒ ሞሮኮ ላይ ዝግጅቷን ከቀናት በፊት መጀመሯ ይታወቃል። በምድብ አራት ከኢትዮጵያ፣ ግብፅ እና ማላዊ ጋር የተደለደለችው



የምዕራብ አፍሪካዊቷ አገር ጊኒ አሠልጣኝ ካባ ዲያዋራ ከቀናት በፊት ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ ያደረጉ ሲሆን፣ ከግብ ጠባቂው ካማራ ሙሳ ውጭ በስብስቡ ሁሉም ተጫዋቾች ከአገር ውጭ የሚጫወቱ ናቸው።

የቡድኑ አሰልጣኝ ካባ ዲያዋራ ከዋልያዎቹ ጋር የሚደረጉትን ሁለት የደርሶ መልስ ጨዋታዎች አሸንፈው ሙሉ ስድስት ነጥብ እንደሚወስዱም ተናግረዋል፡፡

ሁለቱን የደርሶ መልስ ጨዋታዎች አስመልክተው ከጋዜጠኞች ጋር ቆይታ ያደረጉት አሰልጣኝ ዲያዋራ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንን በሚገባ እናውቀዋለን፣ በምናውቃቸው መጠንም ተዘጋጅተናል" ብለዋል፡፡

« የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከዘጠና በመቶ በላይ በአገር ውስጥ ሊግ በሚጫወቱ ልጆች የተገነባ ብሔራዊ ቡድን ነው፤ የባለፈው የቻን ውድድር በደንብ እንድናያቸው ዕድል ፈጥሮልናል፣ ኳስ ይዘው መጫወት ይፈልጋሉ፣ ብዙ ይሮጣሉ፣ ሶስቱንም ጨዋታዎቻቸውን ተመልክተን ለነሱ የሚሆን ታክቲክ አዘጋጅተናል፤ ሁለቱንም ጨዋታዎች አሸንፈን ስድስት ነጥብ ከኢትዮጵያ ላይ ወስደን ወደ ኮት ዲቯር እናቀናለን፡፡» ሲሉም እርግጠኛ ሆነው ተናግረዋል።

ከሜዳቸው ውጭ መጫወታቸው በውጤቱ ላይ ልዩነት ይፈጥር እንደሆነ የተጠየቁት አሰልጣኙ ሲመልሱ፣ ሞሮኮን የመረጡት ሁለቱም ፌዴሬሽኖች በስምምነት መሆኑን አስረድተዋል። ጨዋታዎቹ የሚካሄዱት የረመዳን ጾም ወቅት በመሆኑም ቡድናቸው በመሃል ጉዞ ሳያደርግ መጫወቱ ጥቅም እንደሚኖረውና የትራንስፖርት ወጪም እንደሚቀንስ አክለዋል። "በርካታ ጊኒያውያን በሞሮኮ እንደመኖራቸው በኛ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖራል ብዬ አላስብም፣ ዋናው ነገር በርካታ ጊኒያውያውያን በስታዲየም ተገኝተው ጨዋታውን እንዲመለከቱ መጋበዙ ላይ ነው" በማለትም አሰልጣኙ አስተያየት ሰጥተዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

በሰመራ-ሎግያ ከተማ መስተዳድር በ2015 ዓ.ም በጀት አመት በሰመራ የወድበይቱ ጤና ጣቢያ ግንባታ ስራ በያዘው በጀት መሰረት በዘርፉ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸውን አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል።

**ስለዚህ በጨረታው ለመወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተገለጹትን ነጥቦች በማሟላት መወዳደር የምትችሉ ሲሆን፤**

1. ተጫራቾች ግዴታ ማሟላት ያለባቸው የቅድሚያ መወዳደሪያ መስፈርቶች ማለትም፤

1.1.1. በዘርፉ በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው።

1.1.2. ከሚፈለገው አገልግሎት ጋር የተዛመደ የንግድ ስራ ፍቃድ ያላቸው።

1.1.3. የንግድ ፍቃድ ምዝገባ ሰርተፊኬት ያላቸው።

1.1.4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝባ ሰርተፊኬት ያላቸው።

1.1.5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ( TIN ) ሰርተፊኬት ያላቸው።

1.1.6. የጨረታ ሰነድ ግዥ መፈጸም የሚችሉ መሆን አለባቸው።

2. ተጫራቾች ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 30 ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት የሰመራ-ሎግያ ከተማ መስተዳድር ፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ውስጥ የግዥና ንብ/አስ/የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 105 የማይመለስ ብር 500.00 ( አምስት መቶ ብር ) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ትችላላችሁ።
3. ተጫራቾች በእያንዳዱ በሚያቀርቡት የጨረታ ሰነዶች ላይ የተጫራቾች ወይም የህጋዊ ወኪል ፊርማና ማህተም ሊኖራቸው ይገባል።
4. ማንኛውም የጨረታ ተወዳዳሪ በሚያቀርበው የጨረታ ሰነድ ኦርጂናልና ኮፒ በተለያየ ፖስታ በማድረግ ሁሉንም በአንድ ፖስታ ላይ ማድረግ ያለበት ሲሆን 1 % ጨረታ ማስከበሪያ ሲ.ፒ.ኦ/ CPO/ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያው ጋር አብሮ ማቅረብ አለበት።
5. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ከማንኛውም ተጫራቾች የሚቀርብን የውድድር ጥያቄ መ/ቤቱ አይቀበልም።
6. ጨረታው ማስታወቂያው ከወጣበት ጀምሮ ተከታታይ ባሉት 30 ቀናት የሚቆይ ሆኖ በእለቱበ31ኛው ቀን ማለትም ሚያዝያ 12/2015 ዓ.ም ከጠዋት 4፡00 ሰዓት ላይ የጨረታ ሳጥን የሚዘጋ ሆኖ በእለቱ ከግማሽ ሰዓት በኋላ 4፡30 በከንቲባው ፋይናንስ ጽ/ቤት የግዥና ንብ/አስ/የስራ ሂደት ክፍል ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በይፋ ይከፈታል።
7. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
8. **ስተጨማሪ መረጃ በቢሮችን በአካል በመቅረብ ወይም በቢሮ በስልክ ቁጥራችን 033 666 0583 ደውለው ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።**

**በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰመራ-ሎግያ ከተማ መስ/ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት**

## ብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ስልጠና ሽፋን የሚሰጥ የመፅሔት ህትመት ግዥ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የግዥው ዓይነት | የጨረታ ሣጥን የሚታሸግበት ቀንና ሰዓት | ጨረታው የሚከፈትበት ቀንና ሰዓት | የግዥ መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የመፅሔት ህትመት ግዥ | መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት | መቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:05 ሰዓት | DBE/NCB/ PR/004/2022/23 |

**የጨረታ ማስከበሪያ መጠን**

| ተ.ቁ | የጨረታ ማስከበሪያ መጠን |
|---|---|
| የሁለተኛ እና የሶስተኛ ዙር የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ስልጠና ሽፋን የሚሰጥ የመፅሔት ህትመት ግዥ | 20,000.00 በሲ.ፒ.ኦ(CPO) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ህጋዊ ከሆነ ባንክ |

1. ተጫራቾች ከጨረታው መልስ ጋር የሚከተሉትን ተጨማሪ ሰነዶችን ያቀርባሉ።
- በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/
- የግብር ግዴታ ለመወጣቱ ከሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት የተሰጠ ተጫራቹ የግብር ግዴታ የተወጣ በመሆኑ ጨረታ ላይ መሳተፍ እንደሚችል የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ (ጊዜው ያላለፈበት መሆን ይኖርበታል)
- የተ.እ.ታክስ VAT ሰርተፊኬት
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የአቅራቢዎች ምዝገባ ሰርተፊኬት
- የማጭበርበር ድርጊት ላለመፈጸም ቃል የሚገባበት ፎርማት ተሞልቶ የተጫራቹ ድርጅት ፊርማና ማህተም የተደረገበት

2. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር/ሰነድ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00 /ብር ሁለት መቶ/ ታወር አንድ በባንኩ እግረኛ መግቢያ ክፍያውን ፈጽመው በባንኩ ታወር ሶስት 1ኛ ፎቅ ከግዥ ቡድን ቢሮ መውሰድ ይችላሉ።
3. የጨረታ ሰነድ ለተጫራቾች መሸጥ የሚጀምረው ጨረታ አየር ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ ከመጋቢት 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ነው።
4. ተጫራቾች የሚያቀርቡትን ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው መጀመሪያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከላይ በሰንጠረዥ እስከ ተገለፀው ቀን እና ሰዓት ድረስ በባንኩ ታወር ሁለት መግቢያ ላይ ለዚሁ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ኦሪጂናል እና ኮፒ በተለያየ ፖስታ በማሸግ ማስገባት ይችላሉ።
5. ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት የህትመት ዓይነቶች በባንኩ የቀረበውን ናሙና መመልከት እንዲሁም ተመሣሣይ ህትመቶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
6. አሸናፊው ተጫራች በተፈለገው ጥራት መሠረት የህትመት ግዥውን ገቢ ካላደረገ ባንኩ ህጋዊ እርምጃ የሚወስድ በመሆኑ ተጫራቾች ይህንን ከግንዛቤ አስገብተው ናሙና ከጨረታ መከፈቻ ቀን በፊት መመልከት እንዲሁም ተመሣሣይ ህትመቶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
7. ጨረታው በሰንጠረዡ ላይ በተገለፀው ቀንና ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
8. የጨረታ ሰነዱ ቋንቋ አማርኛ ነው ባንኩ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ስበለጠ መረጃ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ታወር ሁለት 5ኛ ፎቅ በሚገኘው የግዥ ዳይሬክቶሬት በግንባር በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 0115578088 የውስጥ መስመር 364 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።**

**የኢትዮጵያ ልማት ባንክ**